# ከራስ ዳሽን ግርጌ

## የግጥም እና የአጫጭር ልብ-ወለዶች መድብል

በዓሊ. ዓለሙ ሃሰን

ሐምሌ 2008

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

ከምፒውተር ፅሁፍ

መሳይ ጫኔ

ግራፊክ ዲዛይን

መሳይ ጫኔ

የመጀመሪያው ዕትም፡ ሐምሌ 2008

Copyright @2015 by Ali Alemu Hassen

***ስለመፅሃፉ ያልዎትን ማንኛውንም አስታየት

በኢ-ሜል አድራሻዬ ሊያደርሱኝ ይችላሉ

Alihassen62@yahoo.com





# መግቢያ

አቅሜ በፈቀደው ያያሁትን የሰማሁንት የቀመስኩትን ያሸተትኩትን በራሴ የአገለለፅ ዘዮ እምነጭራለሁ.............ይህ ማለት ለአቅመ ደራሲነት ደረሺያለሁ ብየ በልበ ሙሉነት መናገር ይከብደኛል።ነገር ግን ላሳደገኝ ማህበረሰብ ምስክርንቱን ከእኔ በላይ መናገር የሚችል እንደሌለ ግን በእርግጠኝነት እናገራለሁ።ባህል እና ወጉን አጣብቶ ያሳደገኝ ህዝብ በማርያም ሲሉት የማይጨክን ሩህሩህ እና አዛኝ ባለማህተብ ማህበረሰብ ደግነቱን፣ይቅር ባይነቱን፣ጀግንነቱን ባአጠቃላይ ማንነቱን በማንነቴ ውስጣ አሻራውን አሳርፏል።በዝህ መፅሃፍ ውስጥ የአካተትኳቸው አጫጭር ልብ-ወለዶች ይብዛም ይነስም ካየኋቸው እና ከሰማኋቸው እውነተኛ ታሪኮች እምብዛም አይርቁም

# ምስጋና

አይዞህ በርታ ላሉኝ ጓደኞቼ በሙሉ........ጊዜውን አጣበና እንቅልፉን ሰውቶ ይህንን መጽሃፍ ከዚህ ላደረሰው ለመሳይ ጫኔ፣ሙያዊ ትችት እየሰጠ ለመጽሃፉ ጥንካሬ የበኩሉን ድርሻ ላደረገው ለገጣሚ በቃሉ አዳነ ...........እንዲሁም በአትላንታ የሎሬት የኪነ-ጥበባት ማዕከል አባላት ምስጋናዬ የላቀ ነው።ከአሁን በፊት ባሳተምኩት የመጀመሪያው ስራዬ ማለትም "እርባ ጅራፍ" የግጥም እና የአጫጭር ትረካዎች መድብል ላይ ማስተካከል እንዳለብኝ የተሰጠኝ ገንቢ ሃሳብ በዝህ ስራዬ ላይ ማስተካከል ሞክሪያለሁ።

በዚህኛውም ስራዬ ላይ ቢሆን መልካም ሃሳባችሁና ድጋፋችሁ እንደተለመደው አይለየኝ እላለሁ

ደራሲው





# ማውጫ

## ስነ-ግጥም

ደጋጎቹ ............ 1
ተሻገርኩ ............ 3
እኔን ............ 4
ይቺን እሞራ ............ 5
ከአይኔ ከብሴኑ ............ 6
ፃፈልኝ ............ 7
አጀብ ............ 8
ትዝ አልሽኝ ............ 9
እኔማ ............ 10
ምስማሬ ............ 11
እኔ አላገባሽም ............ 12
እቦ የእኔስ ከራማ ............ 13
መርፌ ወጊ ............ 14
እየሁሽ ዘንድሮ ............ 15
እንቺን ብየ እኮ ነው ............ 16
እግዜር ብሆን ኖሮ ............ 17
ከድንቡሎ ሳንቲም( 5 ሳንቲም) ............ 18
እጠብቅሻለሁ ............ 19
ያኔ ............ 20
ህልም አለኝ ............ 21
ህዝብ ............ 22
እንግጠም ............ 23
ምን ይሻላል ............ 24
ወይ ጊዜ ............ 25

ጠተን እንገናኝ........ 26

## ልብ-ወለድ

ባለ ከራሩ........ 28
አትላንታ........ 32
የሰለት ልጅ........ 40
እህል ውሃ........ 44
ካሜራው........ 50
ከራስ ዳሽን ግርጌ........ 53
ቅድስት........ 55
በማርያም........ 59
አብዱ........ 62
አርቅ........ 65
ምስጥ........ 68





# መልካም ንባብ

# ደጋጎቹ

ይሄው ጀማመረኝ....ወዘወዘኝ ደግሞ
የሸሆቹን ቂሷ...ሩሃንያውን ቀልቤ ተሸከሞ
ልው አለብኝ ባይኔ......
የወይራው ያድሩሱ....የሉባንጃው ጭሱ
የጀማዓው ሶፋ...ሃድራና መጅሊሱ
የእነ አቢጋር በረከ....ተሰሊም ቡና ቁርሱ
ቀምበጥ መሳሪያቸው....ቱፍታ ማሻሪያቸው
ፍቅር ጨዋታቸው...ጎሜ ጠላታቸው
አፉ በል እያሉ....አፉ በለኝ አፉ
ካልሮጡ አይገኙ....ካልተከለፈለፉ
ወረብ አቦ ውሎ....አውምባ ያደረው
የጁ ካፋፉ ላይ...መድፉን የቀየደው
የተጣላውን ሰው....አስታርቆ ሚሄደው
እያከረተረተ....እያጉረመረመ....ይወርድና አውልያው
ወረም ሰላም ገሸር...ይላል ዘመንያው...ወይም በረኸኛው
አጥግበኝ ይለዋል ...ምታልኝ ድቢውን...ማስገሪያ ዜማውን
ገሸሩ ምን ገዶት........ከዛማ እንዲህ ይላል
አውሊያው በረኸኛው....በረኸኛው
ሰበር በረኸኛው.....በረኸኛው
ብሬም ይሆን እንጃ....ሃብቴም ይሆን እንጃ
ሞሪድ ይሆን እንጃ.....ሰይፌም ይሆን እንጃ
ጀሚል ይሆን እንጃ.....ጎሸም ይሆን እንጃ
ቁሟል ከበራፉ.....ባላጭር ጠመንጃ
ሰላም ዋል ወዳጀ....ሰላም ዋል ከመርሳ
ማን አገናኘብኝ....ሁለቱን አንበሳ
አዳል ከገናሌ....ወሰየን ካወሳ
ላነፈነፈው ዛር....ላኮረፈው አውሊያ
ይለማመኑታል...ያሞጋግሱታል...
ይቅር በል እያሉ....አባ ሰበር ጓያ
የሸሆቹ ውርፍት....ዋሪዳው ሲገባ

ሃብት ለፈለገ....ገንዘብ ጀባ ጀባ
ጤና ለፈለገ....አፈያ ጀባ ጀባ
አሜን ሸሆቻችን....ይሁን መረሃባ
ሁሉም በመደዱ.....እንደየመጣበት ሃጃው ሁሉ ወጦ
በበረከ በዱዓ...በአበጋር ምርቃት...በሃድራ ተንዳፍጦ
የታመመ ሸሮ...ያጣውም አግኝቶ...
ሰውም...አውልያውም....ያድራል ተሸኝቶ
እኔም ዛሬ እንግዲህ.....
በደጋጎች መጀን....ሃየ ልበልና
ከጤናው...ከአርዚቁ...ከእድሜ በረከቱ
ሁሉን ይስጡኝ እና
አሰላም ማሊኩም ብየ እመለሳለሁ....ነገም እንደገና





# ተሻገርኩ

አንዳንዴ ይህ ቀልቤ.....ይዋዥቅብኛል
የ44ቱን መንደር....ይናፍቅብኛል
የትዝታ ቁስል....ናፍቆት አመርቅዞ
ጎንደር ልደታ ላይ....እያደረ አዘዞ
ይከፋኛል ደርሶ....ይጎተጉተኛል
ሰፈሬ ከፊቴ...ድቅን ይልብኛል
አላቋርጥ ውቅያኖስ....አልበር እንዳሞራ
እርመጠመጣለሁ....ከሰመመን ጋራ
አቤት........
ጎንደር ሸንተረሩን....ጎንደር ደና ደኑን...ተሸከሞ ቀልቤ
ሁሌ እቃትታለሁ....ይደከማል ጉልበቴ...አልሄድ እንደ ልቤ
ከድጓው ከቅኔው...ከማህሌት ዘግና
ወረብ ሸብሻቦውን...መዝሙር አቀንቅና
ድባብ በወርቅ ካባ....ታቦት አሸሞንሙኖ
የመስጊዱ ጥሪ....አዛን አላዝኖ
ያሳደገኝ አድባር....የደጋጎች አገር
የሁሉ እናት አገር...ስታንፍቀኝ ጎንደር
እንዴት እንቅልፍ ወስዶኝ....እፎይ ብየ ልደር

# እኔን

እኔን እኮ.....
ሳልደርስበት ስንቱ....ይጠነቁለኛል
የያዝኩትን ልውሰድ...ልቀማህ ይሉኛል
እንደ ጅል...እንደ ቂል..ሊያዩኝ ያምራቸዋል
በእኔ ተጠልለው...ይታከኩብኛል..ያነፃፅሩብኛል
ልምከርህ ይሉኛል.....ላንተ ነው ይሉኛል
.........እኔን
ይህን ባወኩ ጊዜ ለመራቅ ስሞክር...ይከታተሉኛል
ወሬ ባጡ ጊዜ...የእኔን ስም አንስተው...እንዲህ ነው ይሉኛል
......እኔን
እኔው ለወደድኩት ...እኔው ለተመቸኝ
እዩትማ ልቡሱን...እዩትማ ፁጉሩን...ታራራም..ይሉኛል
ምን እንደምሰራ...ከማን ጋር እንደዋልኩ...ይቆጣጠሩኛል
.......ሳሳዝን......እኔን
ባልዋልኩት አውለው...ስሜን ያጠፉታል
እኔን ሳልጨነቀኝ...ይሟገቱለታል
......እኔን...ወርዶብህ
ብልጦቹ...ብስሎቹ...መቸም ጊዜ አላቸው
ስለ እኔ መፈትፈት....ሆኗል መዋያቸው
....አቤት.....
እንዲህ ያለ ነገር ተይዟል አቦ.......





# .......ይቺን አሞራ

እያቹህልኝ ወይ....ሰጎኗን አሞራ
ሰብራው ሄደች ጎኔን...ያጥምቴን ወጋግራ
አሁን ወጣች አሉኝ...አምራ ተሽቀርቅራ
ያንዱን ቤት ልታፈርስ....ያንዱን ቤት ልትሰራ
ጎበዝ ጀግና ልትማርክ...ወግታ ባይኗ ጭራ
ያዙልኝ ይቺን ዕብድ...ቀልብ የለሽ መለሎ
እሰሯት በገመድ....ጣሉልኝ በቶሎ
አይን እግሮቿ ሴባ....ሰው ሚጎነትሉ
እየጎፈጨፉ...እየቦነጨፉ...ስንቱን አቆሰሉ
ስንቱን እየነኩ...ስንት ልብ አስጣሉ
ይቺ የወፍ ቡዳ.....ደም ቀማሽ አሞራ
ወሰደቺው ልቤን...ቆርቁራ መንቅራ
በሰው ባደባባይ....በቀን በጠራራ

## ከአይኔ ከብሌኑ

በዛቺ ገጠር መንደር...ከለምለሟ ሜዳ
ዛፎች ውስጥ ባለቺው...በሳር ቤቷ ጓዳ
ያኔ በጮርቃነት...ያየሁሽ እንግዳ
መለሎ ቀንበጥ ልጅ...ቅብጥብጥ ጉድሮ
ያንቺ አቋም በእኔ ውስጥ...እየኖረኝ አብሮ
ተቃልመሽኝ ቀረሽ...ከአይኔ ከብሌኑ
መቸ እንደማገኝሽ....ራቀብኝ ቀኑ
ነይ እጀ ሙሉ ነው...እቀበልሻለሁ
አምባር ነጭ ጥላውን...አመጣልሻለሁ
ድሪ ቀለበቱን....አልቦ ቀይ ጥለቱን
ድባ ስንድድሽን...ማርዳ ወለባውን
አሸን ከታብ ኩሉን...ቀድሰም ጡሩራውን
ሁሉን መሳሪያሽን.,...እገዛልሻለሁ
ዘንድሮ አሳጭቸሽ...ከርሞ አገባሻለሁ
ጋሜ እና ቁንጮሽን....ቀቢ አደስ ቅቤውን
አንሶስላ ለእጅሽ....ሻሹን ለወገብሽ...ደርቢ ሞራውን
ከዛማ..................
ጋን ጠላ አስጠምቀን....ሰንጋ በሬ ጥለን
ከበሮ አሲደልቀን...ጡሩንባ አስነፍተን
ሆታ እና ፍከራ....ጥይት አስተኩሰን
የሽማግሌ እግር...ስመን ተመርቀን
ወግ ማዕረግ....አድርሰን
አብረን እንኖራለን እስከዘላለሙ....እንደ ሻማ ቀልጠን





## ፃፈልኝ

ፃፈልኝ ደብዳቤ...ውድየ የእኔ ፍቅር
ወረቀቱን እንዳንቺ...አቅፌው እንዳድር
አንቺ እንዴ ፅፈሽው...የላከሽውን ፖስታ
እነብልሻለሁ ...ባልሰለች ጧት ማታ
እኔም እፅፋለሁ...እምነጭራለሁ
እለቀልቃለሁ....እፎነጭራለሁ
አሁንም አሁንም...በህልሜም በዕውኔም
ደሜ ውስጥ አንቺው ነሽ....ሌላ ማንም የለም
የእኔ የውበት ፀዳል....አደይ አበባየ
ፍቅርን ምቧርቅብሽ...ለምለሟ ሜዳየ

ውብየ...ናፍቆቴ....የወይን ጠጅ ሳሬ
አገር አበደ አለኝ....በፍቅርሽ ሰክሬ

.....እኔም አልኳቸው....እሰየው

ያንቺው ተመኝቶ

# አጀብ

እንዲያው ይሄ ቀልቤ....ስንቱን ያስታውሳል
ትላንትን እያየ...አደቤን ይነሳል
ከቆረጠው እሸት...ካሻቸው ዘለላ
ከጠነቆለው ማር...ከዋጠው ወለላ
ከለቀመው ፍሬ....ካንጠባጠባቸው
ከቀማመሳቸው....ከጠረጠራቸው
ዶለኝ ወስዶ ቀልቤ...ጎትቶ ከኋላ
የድሮውን ሳስብ...እንዴት አሁን ልብላ
..........አጀብ
የዘመኑ ፍጥነት....የጊዜው ሩጫ
እድሜ መንገደኛው...ጠፋበት አቅጣጫ
.......እስኪ ይሁና
ትዝታም ይኮምኮም....እንጀት ከጠገነ
ቀልብ አደብ ከገዛ....በነበር ከሆነ





# ትዝ አልሽኝ

አጀብ ያንቺስ ህልቂያ.....
አጀብ.... አጀብ ....አጀብ
አጀብ ነው አንቺየ
ውዴ ዘመናየ...ፍቅሬ ትዝታየ
መገን መገን መገን....መገን ወሎየዋ
እንዴት ነሽ ባኢያሌው...እንዴት ነሽ አንቺዋ
ልቤ ዘምቶ እያለ...ደሴ ሙጋድ ገቢያ
አድራሻሽ ጠፍቶብኝ....ወጥቸ ወልድያ
አምባሰልን ዞሬ....መርሳን አካልየ
ሃይቅ ላይ አድሬ...አንቺን አገኝ ብየ
አረብ ገንዳ ጢጣ...ዳውዶ ላይ ውየ
ብጠይቅ ባስጠይቅ...የሚያውቅሽ አጥቸ
እንደ ሃረጎው መንገድ...ቀልቤ ተጥመዝምዞ
በሃሳብ ወርጀ
ቦርኮና ድልድዩን...በጧት አቋርጨ
ቤትሽን አገኘሁት...ከመናህሪያው ጎን...ኮምቦልቻ ገብቸ
እንዳንቺው እየሩ....ነፋሻው ማማሩ
እየሁሽ ወርቄዋ....ቆማሻል ከበሩ
ላናግርሽ ፈርቸ....ተመልሽ ሄድኩኝ...ልመለስ አቅጀ
ግን መቸ ተሳከቶ...እንደወጣሁ ቀረሁ...ከአገሬ ወጥቸ
እንታለምዋ....መርከቤ...ባቡሬ
ወርቄዋ....ማሬዋ
መጋሌ መጋሎ....ቆንጆት ወሎየዋ
እንዴት ነሽ ባያሌው...ልቤን ነጣቂዋ

.

.

ማን ያውቃል....እመለስ ይሆናል

# እኔማ

ዳሸን እና ጉና የእኔ አልነበሩም ወይ...አፈጣጠሬማ
ከእነ ጎጡ ብርቄ ወረወረኝ እንጅ...እድሌ ሆነ እና
ታዲያ ይሄው......።
ሰው ጋር ተሰትሬ...ሰው ሰው ይርበኛል
ልቤ እየሸፈተ....ከጎኔ ይርቀኛል
ባልተከሸነ ወጥ....ባልቦካ እብሲቶ
ሹራር ሆዴ አሾረ...እንጀቴ ሸብ





# ምስማሬ

.....ስንት ጊዜ መከርኩሽ....ነገርኩሽ ሰበኩሽ
ወገብሽ ላይ እጥፍ...ማለቱን አብዝተሽ
እንሆ ዛሬ ላይ...ዱልዱም ብለው ጣሉሽ
እኔም እንደ እነሱ...በቆሙት ቀየርኩሽ
እንያያዝ ብየ... ነበር የወገርኩሽ....በእጀ የደገፍኩሽ
እልገባም አልሽና እጥፍ ብለሽ ድንገት...ይሄው ጎብጠሽ ቀረሽ.....
መያያዝ ማያያዝ....መቸም አላለልሽ....
ማርቴሎም መዶሻም....ከእንግዲህ አይነኩሽ

መጥመም ..ማስወርወሩን...ማስጣሉን ረስተሽ

# መርፌ ወጊ ብሆን

መርፌ ወጊ ብሆን....ሃኪም ጥበበኛ
አወጋቸው ነበር....በቁም ሳላስተኛ
ጉንፋንም ላመማት....ለቆረጣጠማት
ውጋት ወጋኝ ላለች....ራሷን ላመማት
ለሁሉም መድሃኒት....ቶሎ ሚያሽላቸው
ለዛቹም ለዝቹም....መርፌ ሳዝላቸው
ዳሌያቸውን በእጀ.....ስነካካላቸው
ተመስጌን ትል ነበር....ምስኪኗ ነብሳቸው
በጥጥ እያዋዛሁ...ጣውላ እና ገምሻሬን
እሰገስግ ነበር....ወደ ውስጥ መርፌየን
መርፌ ወጊ ብሆን........
ወረርሽኝ ቢገባ...የቆንጆ በሽታ
አወጋቸው ነበር...ውጋን ያሉ ለታ
ይወራልኝ ነበር.....እጀ መድሃኒቱ...ሃኪሙ ተብየ
ያቺንም ይቺንም...ገልቤ ስወጋ...በእይዞሽ እባብየ
መርፌ ወጊ ብሆን.......
ከታፋዋ በታቺ...ያን ስጋ ዘግኘ
እሸኛት ነበረ....እሷ ተፈውሳ...እኔም በእሷ ድኘ...





# አንቺን ብየ እኮ ነው

እቴ ያገሬ ልጅ...ውዴ የደም ገንቦ
እንዳላይሽ በየት...ዙሪያሽን ሰው ከቦ
አንቺን ነው የሚያዩ...አንቺን ነው ሚያደምጡ
ካልበላሽ አይበሉ...ካልጠጣሽ አይጠጡ
እኔም እንዱ ሆኘ....አግኝቶኝ መጋኛሽ
እከተልሻለሁ...ከጀርባ ከኋላሽ
ትወጃለሽ ቢሉኝ...ንክር የሰው ጥሬ
ፍቅሬ መጣሁልሽ...ፀጉሬን አነፍሬ
አጠር ባለው ጉርድሽ...ፈርጠም ባለው ጭንሽ
በምኞት ሰልስየ...ቆሜ ቀረሁልሽ
መንገድ ላይ አንቺ ነሽ...የትም የት አንቺ ነሽ
ሰው እንደ ቀጤማ.....ተነሰነሰልሽ
እኔም እንዱ ፍሬ...የሳሩ ዘለላ
ወድቄልሻለሁ...ባንቺ እሳር ልበላ
እገፈተራለሁ...ውጣ ሂድ ይሉኛል
ለአይነ ሥጋ ቀንተው...ያሟርቱብኛል
ያደለውስ እቴ...አንቺን ግብረ ሥጋ
መቾም ትኩስ ገላሽ...ሳቱም አይስጠጋ
ብቻ እመኝሻለሁ...አገር እስከትለቂ
ወይ አጭር ጉርድሽን...ለእኔ እስከታወልቂ...

# እግዜር ብሆን ኖሮ

ተዳፈርከ አትበሉኝ...አደራ እባካችሁ
ምኞቴን ለመግለፅ...እንደሆነ እውቃችሁ
ይቅር በለው በሉኝ...ይቅርም እንዲላችሁ
እኔ ያንተ ፍጡር...ኢትዮጵያዊ ያረከኝ
ተመስገን ብያለሁ...ነገሩ እያሳቀኝ
እኔ እግዜርን ብሆን...አንዳንተ ቢያደርገኝ
ኢትዮጵያን ወዳጆን...ማደርግላት ታየኝ
ያማኑኤል ወዳጅ...አንተን ለሚዘክር
እምየ ድንግልን...ብሎ ሚመሰክር
ለገብርኤል ለባህታ...ጧፉን ለሚያበራ
ዳዊት ኪዳን ገልጦ...ስምከን ለሚጠራ
አቤት እግዜርየ...እኔ አንተን ቢያደርገኝ
ለወዳጆ ምላሽ...ደግነቴ ታየኝ
የሞሚንየ አገር....የወልዮች መንደር
መውሊድ የሚያወጣ...መስጊድ ውሎ ሚያድር
የእሙየን ልጅ አንዱን...የነብዩን ወዳጅ
ሳይኖረው በባዶው...ሚዘይር ኡምራ ሃጅ
እኔ አንተን ....ቢያደርገኝ
የማደርገው...ታየኝ
በወንዞቿ ቁጥር....ነዳጅ እንዶልዱየ
ተራራ ገደሉን...ወርቅ አልማዝ አብቅየ
እውቀት የተባለን...ሰጥቸ ሰጥቸ
ሰይጣን በዛ እንዳይደርስ...ካገር አስወጥቸ
ፍቅርና ሰላምን....አብዝቸ አብዝቸ
ከፋትና ተንኮል...ስርቆት ሴት አዳሪን
ምድረ ገፅ አጥፍቸ
ከማቱሳላ እድሜ...ቆንጥሬ ሰጥቸ
እሰጣቸው ነበር.....ለእኒህ ወዳጆቸ





# ከድንቡሎ ሳንቲም (5 ሳንቲም)

ከድንቡሎ ሳንቲም.....
ጠመንጃ እንደያዘ ከቆመው ሰውየ
ከጀርባው አንበሳው አፉን ከፍቶ እያየ
ሰውየው ሳይተኩስ...ሳያገሳ አንበሳ
ባደጉበት መንደር...መሳና ለመሳ
አንዱ አንዱን ሳይነካ አብረው እንደኖሩ
በፍቅር በሰላም በገቢያ እንደዞሩ
በመቻቻላቸው....ስንቱን እንዳከሩ
ድምቡሎ ስትከዳ...ካገሯ ስትወጣ
ሰውየው ከቀየው...አንበሳው ከዱሩ
ዘመን ከፍቶባቸው...እንደወጡ ቀሩ
ምስኪን 5 ሳንቲም.....

# እጠብቅሻለሁ

አለም ከወደድኩሽ...ልቤ አንቺን ካኖረ
ዘመኑ ነጎደ...ስንት አመት ቆጠረ
ከእኔ እና አንቺ ኋላ...ካሰብኩሽ ጀምሮ
ተወልደው ያደጉት...ትዳራቸው ሰምሮ
እኔ ቁሜ ቀረሁ.....አርግዥሽ በሆዴ
ለመሆኑ እንዴት ነሽ...ጤናሽን ዘመዴ
አገባሽ ወይ ወለድሽ....ወይስ ቁመሽ ቀረሽ
እንደ እኔው ጥሎብሽ...ቀንሽን እየቆጠርሽ
ለሰው ሁሉ ነገርኩ...የማፍቀር ዲካየን
የመውደድ ጣራየን
ቁልቁለት ጥልቀቱን...ዳገት ርዝመቱን
ተናገርኩ ላገሬው...ልቤ አንቺን ማጣቱን
ያንቺ ድርቅ እንጉዶት..ጉድ ሆኖ መቅረቱን
መጀን ብየው ነበር...ያገሬን ከራማ
ምናልባት ችግሬን...ብሶቴን ቢሰማ
እጭሽ እጫጭሽ....ወገርት እና ውግዙን
በማዕናው ወንጭፍ....ልኬብሽ ያለቱን
ወይ ፍንከች አለሜ...ዘመን ተቆጠረ
የጠቆረው ፀጉሬ...ሽበት ጠረጠረ
እጠብቅሻለሁ....ከሰጠኝ ከአዱኛው...እፌትና እድሜውን.....
ፈርዶብኝ የለም ወይ....ሰ'ቶ ዋሪዳሽን...ፍቅር ሙሃባውን





# ያኔ

የልጅነት ፍቅር...በዳበሳ ዳዴ...በሽምጥ ጋላቢ
የእምቡጥነት እድሜሽ....ስጋ ነብስ ሰላቢ
አፍላ ጉርምስና ..እንደ እሳት ገሞራ..ልብ እያናወጠ
ድህነት የሚሉት ከፉ ወደረኛ...ኪሴን እየናጠ
ይዥሽ እወጣና በባረቀው ፀሃይ..ሙቅ ውሃ እጋብዝና
ወይ ደግሞ ካለቺኝ ሽልንግ ሜዞ ቢጤ..ሚስጥር ኪሴ ካዝና
አንቺን ለማስደስት...ሰውም እንዲያይልን መዝናኛችን ቦታ
አራዳ መተና...ወይ ደግሞ ደልሽየስ የገባን እለታ
አቤት ጉድ ኩራቴ የልቤ መደንደን...የውስጤ ደስታ
ፓፓያ አቦካዶው..ከቦንቦሊኖው ጋር...ጭማቂው ሲመጣ
ያቺን ተጎራርሰን..በማንኪያቿን ዘግነን...ልሰን ተላልሰን
ከእኛ በላይ ማን ሰው...መሃል አራዳ ውስጥ ፒያሳ ላይ ተዝናንተን
ደግሞ እንወጣና...እጀን በእንገትሽ ውስጥ በጥምጥም አቅፌሽ
ከነፋሻው አየር ከፍቅሩ ጨዋታ...አዝለሽኝ አዝየሽ
ምስማር ባያያዘው በተጥለፈለፈው...ደንቀራው ጫማየ
አንቺም በሲልፐር...በክርኔ ጥላ ስር..ገብተሽ በጉያየ
መቺም ሆቴል አንይዝ...አልወስድሽ ፎገራ
እንወጣ ጎሃ....አልወስድሽ ተራራ..አላስገባሽ..ቋራ
ከጠበበችው ዶርም...ከወደቀች ፍራሽ..እንፋረሽና
የኮሲን ባህር ዛፍ...ከማይጠገበው...ከሙዚቃው ቃና
ብብቴ ውስጥ ገብተሽ...ብብትሽ ገብቸ ስንምግ ወዘና
ከመሬት ተመጥቀን...እየተንሳፈፍነ...በጉም በደመና
መጥምጨሽ...መጥምጠሽ...ተመጣምጠን በጣም ከንፈራችን አብጦ
አይኖቻችን በዘው...ጉልበታችን ደከሞ...ልሳናችን ዘግሞ
ያኔ ያሳለፍነው...የልጅነት ፍቅር...ምናብ ታሪካቺን
ታላቅ ትዝታችን.....ጣፋጭ ህይወታችን
ላይመጣ ላንደግመው...ዳግም እንደገና
ሁሉም ነገር ከንቱ...አላፊ ነውና....

# ህልም አለኝ

ህልም አለኝ....ካለልኝ...ከረዳኝ
ምኞቴን...የልቤን...አንድየ ካየልኝ
አልበላኝ ያለው...አልዋጥህ ምግቡ
አልጠጣህ ያለኝ....አልወርድ እንደልቡ
ፍቅርሽ...ፍቅርሽ...ፍቅርሽ...የሰራብኝ ቤቱን
ምኞት...ምኞት...ምኞት.....ያማረው ገላሽን
ህልም አለኝ አንድ ቀን......ይደርሳል የልቤ
እንዳሻኝ ላደርግሽ....ደግሞ እንደሃሳቤ
አደባብስሻለሁ....አጥብቄ አቅፍሻለሁ
ከንፈር እንትንሽን....እመጠምጣለሁ
ፀጉርሽን በእጆቼ....አፍተለትላለሁ
ጆሮሽ ሥር ገብቼ....እንሾካሽክሻለሁ
እንዲህ ሁን እንዳልሽኝ....እሆንልሻለሁ
አንገትሽ ገብቼ....ያመኩትን ብሶት...አለቅስልሻለሁ
እንባየን በእጆችሽ.....አስጠርግሻለሁ
ብቻ ህልም አለኝ........
ይሆናል እመኝኝ....ሳለ ፈጣሪየ....የልብ ንፅህናየ
3 ቀን ፆሜን ፁሜ...ለእንብርክክ ፀልየ.....ተፍቆ ክርኒየ





# ህዝብ

በምናብ ሚጠራ...በጅምላ የታለለ
የገዘፈ ቁጥር....ህዝብ የሚባል አለ
ሳይጠጣ ጠጥቶ...ሳይበላ ሆዱ ሞልቶ
እድገቱ ፍጥነቱ....ጡዞ ሰማይ ወጦ
ሁሉም ሚሳሳለት...ሚንገበገብለት
ስውር ሚስጥር ያለው....የተዋደቁለት
ሳያቃስት ዳገት....ሳይሄድ በቁልቁለት
ለአንተ ነው እያሉ....የሚጎስሙለት
የጥርንቁስ መንጋ....አጥምቶ የወጣ
ለአፈ ቀላጤዎች...እንጀራ ያወጣ
በጅምላ ሚጠራ...የተጠቀለለ
በጅምላ የሚሸጥ...ህዝብ የሚባል አለ
ህዝቡ ....ህዝቡ....ህዝቡ
እንዲህ ብሏል...ህዝቡ
ደግፎናል....ህዝቡ
አፍቅሮናል...ህዝቡ
ቆመናል.....ለህዝቡ
ልንሰጥ ነው....ለህዝቡ...
ለህዝቡ...ለህዝቡ
የተሰገሰገ...በትልቅ ጆንያ
ቢጭኑት የሚጫን...በፈረስ በአህያ
በስም ብቻ ገዝፎ...በአካል ግን የለለ
ሰዎች የሚጠሩት...ህዝብ የሚባል አለ....

# እንግጠም

እንግጠም ካልሽ ይሁን...ይጀመር ግጥሚያችን
እንፋለምና...ይፍረድልን አገር...ይታይ ውጤታችን
እንግጠም ካልሽ እሺ.......
ይግጠም ከንፈራችን...ይግጠም ደረታችን
ይስለምለሙ አይናችን....ይግጠሙ እግሮቻችን
ይግጠም ትንፋሻችን...ታቃትት ነብሳችን
እንግጠም ካልሽ እሺ.....
አቅምሽኝ ላቅምሰሽ....እንቃመስ በጣም
ልቤን ብታገኘው...ሆድሽን አላጣም
እንግጠም ካልሽ እሺ.......
እኔ እና አንቺ ብቻ....ሳትፈሪኝ ሳልፈራ
አንዴ አንቺ ከእኔ ላይ...አንዴ እኔ ካንቺ ላይ...እየተፈራረቅን
በተራ....በተራ





# ምን ይሻላል

ባባጥር ብነፋ ባንጓልልም ቃሉእነ

ጌንጭ እንከርዳድ አልለይህ አሉ

# ተይ እንጂ

ከእሱ ከውብ ገላሽ ከፍቅርሽ ዳርጎት ብታቋድሽኝ ምነው

የሚበረከት ሽቱ የሚጣፍጠው ወፍ የቀመሰው ነው

# ባለ እሾህ

እንኮሸሸሌ እና አጣጥ ቀጠጥ አብቃይ

እናጋጠ እሾሁ እንጅ መሬቱም አይታይ

# ወይ ጊዜ

የተሳመ ከንፈር...የታቀፈ ገላ
ስንት ፍቅር ዘግኖ...መውደድ እንዳልበላ
ዛሬ....
ከሺዎች ውስጥ ሆኖ....በብቸኝነቱ...የሩቁን ያስታውሳል
በትዝታ ጥላ....በናፍቆት ሰመመን...ሰጥሞ ያንቀላፋል





# ጠጠን እንገናኝ

ፍቅር ፍቅር አምሮሽ....ፍቅር ፍቅር አምሮኝ
ስቀርብሽ ሸሽተሽ....ሳናግርሽ አፍረሽኝ..እኔም ግራ ገብቶኝ
ሳስብሽ....ሲጨንቀኝ
ጥማትሽ....ሲንጠኝ
እንዲህ እንዲህ እያልነ....ጊዜያችን ነጎደ
ሩቅ ለሩቅ ሆነን....ልባችን ነደደ
አቴዋ.....ኧረ....ለማን ተብሎ
እኔ እንቅልፍ አጥቸ...ያንቺም ልብ ኮብልሎ
ለዚች አፍኝ እድሜ....ነገ ለምታልቀው
ጊዜያችን እንድደን....ፍቅራችን እንሙቀው
አንቺም በዛ ጠጭ....አልኮል አረቂውን
እኔም ከዚህ ልድመቅ....ልሳብ ተኪላውን
..........ከዛማ
ሃፍረት እምቢ የለ....እንዋደቅና
በፍቅራችን በግኖ...ሰይጣን እስኪቀና
የሞቀው ገላሽን...ከጋለው ገላየ
እስከስታ ይወርዳሉ....አሸበል ገዳየ....አሃው ገዳየ
አይናሚት ገዳየ....................
ቀሪ እድሜያችን.....ዘላለሙን
ቀንም...ማታ....ሁሌም...አብረን....አብረን

# ልብ-ወለድ

# ባለ ከራሩ

*አሪ በል ከበሮ*
*አሪ በል ከራር*
*ዓርብ ዓርብ ይቀወጣል*
*መስቀል ፍላውር።*

የትዕግስት ቡና ቤት ዓርብ ማታ እና ቅዳሜ ማታ ከምሽት እስከ ንጋት ሲቀልጥ ያድራል ዲጄ......ባለማስንቆ እና ሲዲዎች ከአገርኛው የሙዚቃ ዓይነት ጀምሮ እስከ እንግሊዘኛ እና "ኦጴራ"...መስቀል ፍላውር በትዕግስት ቡና ቤት በየሳምንቱ ትናጣለች። የውጭ ዜጎች፣ትልልቅ ባለስልጣኖች፣ትልልቅ ባለጠጎች፣የባለጠጎችና የባለሃብቶች ተላላኪዎች፣ከ15 እስከ 40 አመት ዕድሜ ያላቸው ቀይ፣ጠይም፣አጭር፣ረጅም፣ወፍራም፣ቀጭን ሴተኛ አዳሪዎች በትዕግስት ቡና ቤት ግቢ ውስጥ ይሰደራሉ ትግስት ከቡና ቤቱ በስተጀርባ የተንጣለለ ሰፊ ግቢ ያለው ፅዶች፣አበቦች፣ሐረጎች እና በተለያዩ ቁጥቋጦዎች የተዋበ መኖሪያ ቤት አላት።ትዕግስት ብዙውን ጊዜ የምትወጣው ዕኩለ ሌሊት አካባቢ ነው።ወፈር ያለው ቀይ ሰውናቷ ድርያ ልብስ መልበስ ይወዳል ቢጫ፣ቀይ፣ሰማያዊ፣አረንጓዴ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ድርያዎች እሷት ፀጉሯ በዛ ብሎ ረጅም ነው።ከድሪያዋ በላይ የሚያሳሰው ዳሌዋ ከፊት ለፊት የተሰደሩት ጡቶቿዋ አዳም አዳም አዳም ወይ በዚህ ድንቅ ተፈጥሮ አምላክህን አመስግን እያሉ ያስገመግማሉ።ፈገግታዋ ልብን ለሁለት ይከፍላል..........የምትረጨው ሽቶ ከሩቅ ያውዳል።የእግሮቿና የእጆቿ ጣቶች እኩል እንዲሆኑ በጥንቃቄ የተከረከሙ ይመስላሉ፤ምንግዜም ቢሆን ጥፍሮቿዋ በጥፍር ቀለም ያሸበረቁ ናቸው........ ይቺን የሴት ወይዘሮ የማይመኝት የማይለምናት የወንድ ፍጡር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም ከባለትዳር ወንዶች እስከ ወጠጤ ጎረምሶች ድረስ የትዕግስትን ደጅ የማይጠና የለም።ሁሉም ወንዶች ከእሷ ፊት የአቅማቸውን ጡንቻ ያሳያሉ.....ሃብት ያለው ስለ ሃብቱ ስልጣን ያለው ስለ ስልጣኑ ጉልበት ያለው ኃይለኝነቱን ሁሉም ትዕግስትን በፍቅር አንበርክከው የግል ለማድረግ ይባዝናሉ። ለሁሉም ሰው ግራ ያጋባ ጥያቄን ግን የትዕግስት የፍቅር ጓደኛ ማነው የሚለው መልስ ያጣ ጥያቄ ነው።ከትዕግስት ጋር ተኛው ያለ ወንድ ተሰምቶ አያውቅም በእርግጥም ትዕግስት ከማንም ወንድ ጋር አንሶላ ተጋፋ አታውቅም ለጋሿ ለሰው አዛኟ ቆንጆዋ ከራር ወዳጇ ትዕግስት መኖሪያ ቤቷ ውስጥ አንዲት ወጣት የቤት ሰራተኛ እና ጧት ማታ ከራር የሚጫወት አትክልተኛ እሷት ሶስቱ እንደ ቤተሰብ ነው የሚተያዩት እህት እና ወንድም ናቸው ።ባለከራሩ አትክልተኛ ሲበዛ ታማኝ እና ቅን ልጅ ነው።ጠዋት ፀሃይ ብልጭ ስትል ጋሻው ተነስቶ ግቢውን አጽድቶ አትክልቶቹን ውሃ አጠጥቶ በሩ ላይ ጭስ ያጫጭስ እና የሚወዳትን ከራር አንስቶ መጫወት ሲጀምር





ትዕግስት ድሪያዋን ጎትታ ትወጣና የጋሻውን ጨዋታ ታዳምጣለች በፍጹም ትመሰጣለች። ጋሻው ትዕግስት ስትመጣ የምትወደውን ሙዚቃ ይጫወትላታል

ኑኑዬ ገና ሳይሽ ደስ ይለኛል
በበጎ ሃሳብሽ ፍቅርሽ ይመራኛል
ኑኑዬ ኑኑዬ አሃሃሃ
ኑኑዬ ስልሽ አሆሆሆ

ፍፁም ጥልቅ በሆነ ስሜት ዓይኑን ጨፍኖ ይጫወትላታል ትዕግስት በሃሳብ ሰመመን ትሰምጣለች።የጋሻውን ስሜት ትመለከተዋለች ጋሻው ኑኑዬን ይወዳታል።ሰራተኛዋ ቡና አፍልታ ታቀርብላታለች ግቢው በጠዋት ይደምቃል ትዕግስት ከቡናውም ከፀሐይዋም ከጋሻውም ከራር እኩል ታጣጥማለች ውስጧን ደስ ይላታል።ከብዙ ጭንቅ ይገላግላታል።

አንዳንድ ቀን ትዕግስት ከመኝታ በፊት ጋሻውን ጠርታ አንድ ጊዜ ኑኑዬን ተጫወትልኝ ትለዋለች በሰመመን ትነጉዳለች። አንድ ቀን ምሽት ላይ ትዕግስት ጠርታ

"ለምንድ ነው ኑኑዬ የሚለውን ዘፈን እንዲህ የወደደከው"አለችው

" አይ እትዬ ታሪኩ ሩቅ ነው" አላት ዕድሜው ወደ 34 ዓመት አካባቢ የሚደርሰው ቀጠን ረዘም ያለው ጠይሙ ጋሻው። ጋሻው ትዕግስትን በባለጠጋነቷ እትዬ ይበል እንጂ በእድሜ ጠርዝ ቢመዘኑ የሚበላለጡ አልነበሩም።

"ለመሆኑ የት ነው አገርህ "አለችው ትዕግስት

"ወረታ ነው ወረታ የሚባል ሃገር ያልሞከርኩት የስራ ዓይነት የለም በትምህርቴም ደህና ነበርኩ ግና ትንሽ በአቅም ድጋፍ የሚደርግልኝ አጥቼ ይህው እንደወደኩ ቀረው"አላት ትዕግስት ጋሻውን አተኩራ አየችው ይበልጥ ስለጋሻው ማወቅ ፈለገች።

"እስቲ የኑንዬን ታሪክ ንገርኝ" አለችው

"ኑኑዬ ከራቀችኝ ስንት ጊዜው" አለ ጋሻው

"ኑኑዬ የልጅነት ጓደኛዬ ነች በልጅነታችን ዝናብ ሲዘንብ አብረን ራቁታችንን ሩጠናል ወንዝ ውሃ ዋና አዝያት ነበር የምንዋኘው ዕቃ ዕቃ ስንጫወት እኔ ባል ኑኑዬ ሚስት ሆነን ነበር የምንጫወተው ከኑኑ ጋር እየተጫወትኩ ሲመሽ ይጨንቀኝ ነበር። አብሪያት ቁጭ ብዬ ትናፍቀኝ ነበር እሷም እንደዛው የልጅነት ነገር ታውቂው የለ ሁሉ ነገሬን እያየች ሁሉ ነገሯን እያየሁ አብረን ነበር ያደግነው። አንድ ቀን ምን ሆነ መሰልሽ ግን ይቅርታ እትዬ አላት ትዕግስትን።

"እረ ለምኑ ደስ የሚል ታሪክ ነው ዝም ብለ ቀጥል እኔ ደስ ብሎኛል"አለችው ትዕግስት

"ትልልቅ እናቶች ጠዋት ጠዋት ውሃ ይዘው ሽንታቸውን ሲታጠቡ አየሁና እኔም ከኑኑዬ ቤት ሄጄ የኑኑዬን የሽንት መሽኛዋን አጠብኩት"አለና ቀና ብሎ ትዕግስትን ተመለከታት። ጋሻው የትዕግስትን የአግርሞት ሳቅ ጠብቆ ነበር ትዕግስት ግን በመሳቅ ፈንታ ፊቷ ጥውልግ

ብሎ ዓይኖቿዋ እምባ አቅርረው በሃዘን ፊት ዕይታ ነበር የምታየው ጋሻው ድንግጥ አለና "ምነው እትይ ይቅርታ" አለ

"ለምኑ ነው ይቅርታ ጋሻው ይልቁን እትዬ የሚለውን ተወውና ወሬውን ጨርስልኝ"አለችው

"ከዚያም እያጠብኳዋት እያለ የኑንዬ አባት ድንገት ዘው ብለው ቤት ገቡ"

"ማን ነበር ስማቸው የኑኑዬ አባት?"አለች  ትዕግስት በችኮላ

"ጋሽ ፀጋዬ  አዎ ጋሽ ፀጋዬ ይባሉ ነበር"አለ ጋሻው ፈጠን ብሎ

"እሺ ከዛስ ምን ተፈጠረ አለች"ትዕግስት

"ጋሽ ፀጋዬ ያዩትን አላመኑም እኛም ደንግጠን አየናቸው!ጋሽ ፀጋዬ ግን በጣም ጥሩ ሰው ስለነበሩ አቅፈው ሳሙን።ጋሽ ፀጋዬም የሆነው ነገር ሁሉ ለአባቴ ነገሩት የእኔ አባት ግን እኔን ተቆጣኝ..........ጋሻው መሬቱን በእግሮቹ እየቆረቆረ ጋሽ ፀጋዬንም ኑኑዬንም አወዳቸዋለሁ እናፍቃቸዋለሁ ሁሌም ውስጤ ይኖራሉ" አለ "የሚገርምሽ በልጅነት ዕድሜዬ በልጅነት ልቤ ቃል-ኪዳን ከኑኑዬ ጋር ነበረን፤ግና የህይወት ዕጣ ፈንታ ነውና ገና የአንደኛ ክፍል ተማሪ እያለን ኑኑዬን አክስቷ ከእኔ እና ቦርቃ ካደገችበት ሰፈሯ ነጥላ ወደ አዲስ አበባ አመጣቻት ከዛ በኋላ ተገናኝተንም ሆነ ተያይተን አናውቅም የኑኑዬ ፍቅር ግን በልቤ ውስጥ ለዘላለም ይኖራል" ብሎ ከአንገቱ አቀረቀረ።ትዕግስት እንባዋ እየተናነቃት "ከኑኑዬ በኋላ በጉርምስና ሌላ ሴት አታውቅም ማለት ነው?"አለችው ምላሹን በጉጉት የሚጠብቁት ዓይኖቿ እየተቅበዘበዙ።

"እረ በፍፁም በጉርምስናዬ ጊዜ እንጀራ ፍለጋ ነው እንጂ የተንከራተትኩት"አለ እጆቹን ከእጆቹ እያፋተገ

"እንደው አሁን ኑኑዬን ብታገኛት ታገባታለክ"አለችው ሳግና ሳቅ በተቀላቀለበት ንግግር።

"መጀመሪያ ለዓይነ ስጋ ያብቃኝ እና ደህንነቷን ባየሁ ቀሪው ትርፍ ነው"አላት። ትዕግስት ሰቅሰቅ  ብላ አለቀሰችና ጋሻውን ትኩር ብላ እየተመለከተች "እሺ አሁን ኑኑዬን ዝፈንልኝ አለችው?"ጋሻውም ይሄማ ስራዬ ነው

በሚል መንፈስ ከራሩን መደርደር ጀመረ..........."ኑኑዬ ገና ሳይሽ ደስ ይለኛል.........."ከከራር ድርደራው ልቆ የትዕግስት ሳግ ነበር የሚሰማው ጋሻው ድንገት ከራሩን አቆመና "እትዬ ለምንድን ነው የምታለቅሺው አላት?"ለቅሶዋ ውስጡን አረብሾት። "እስቲ ውሃ አምጣና እግሬን እጠበኝ አለችው"ትዕግስት ጋሸው በፍጥነት ውሃ አመጣና የትዕግስት እግር ማጠበ ጀመረ ትዕግስት ልብሷን ወደ ላይ በደንብ ሰበሰበችውና "ጭኔን........ውስጤን ሁሉ እጠብልኝ" አለችው ጋሻው "እረ እትይ ወደ ላይ መውጣት ይከብደኛል"አለ "ጋሻው አልችው ትዕግስት በስስት ዓይኖቿዋ የሚያምሩ ቅንድቦቿን ወደላይ እየሰበሰበች የጀመረከውን ጨርስ እንጂ አንተ የጀመርከውን ማን ይጨርስው ብልክ ነው ኑኑ ነኝ አለችሁ"በተቆረረጠ አንደበት ጋሻው ደነገጠ  በእንዲህ ዓይነት አጋጣሚ አገኛታለሁ ብሎ





አስቦትም አልሞትም አያውቅም ሁለቱም አብረው ሲኖሩ ሁለቱም ተጠራጥረው አያውቁም የልጅነት ፍቅረኛሞች

ኑኑዬና............................... ጋሻው

# አትላንታ

አሜሪካ አሉ ከሚባሉት ትልልቅ ከተሞች አንዷ ጥቅጥቅ ባለው የደን ዛፎች ውስጥ ጥቅጥቅ ያሉ ቤቶች ያሏት አትላንታ ከተማ በውስጧ ከተለያየ አህጉራት የመጡ ህዝቦችንና የአገሬውን ጥቁርና ነጭ ስብስብ አድርጋ የሁሉንም ፍላጎት አሟልታ ይዛላች በዓለም አንደኛ የሆነውን አኳሪየም(Aquarium) ታላቁ የዜና አውታር (CNN)........የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ትውልድ ሃገር (Stone mountain) የሚባል ትልቅ የአለት ተራራ ያላት አትላንታ። ኗሪዎቿ የተቀናጡ መኪኖችን የሚጋልቡበት የተለያዩ ትልልቅ አውራ ጓዳናዎች እነሱም ከተማውን የሚዞረው ቀለበት መንገድ 285 ሰሜን፣ደቡብ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ከታች እስከ ፍሎሬዳ ግዛት የሚደርስ እና 75 ደቡብ እና ከላይ እነ ቴነሲን ፣ኬንታኪ፣ኦሃዮ፣ኢኒዲያናን ዘልቆ ሚቺጋን የሚገባው 75 ሰሜን እና ደቡብ ካሮሊናን ሰሜን ካሮሊናን አልፎ ቨርጂኒያ ግዛት የሚገባው አውራ ጎዳና 85 ሰሜን አልባማ ግዛት የሚገባው 85 ደቡብ እነዚህ አውራ ጎዳናዎች በሙሉ አትላንታን ያገለግላሉ።አብዛኛውን ጊዜ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ6AM እስከ 10AM እና ከሰዓት በኋላ ከ4PM እስከ 6M ከስራ በሚወጣው እና ወደ ስራ በሚገባው ትራፊክ ከተማዋ ትጨናነቃለች።

አትላንታ እያሌ ምግብ ቤቶች፣ መሸታ ቤቶች፣ሲኒማ ቤቶች፣ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች፣ዩንቨርስቲዎች እና የመሳሰሉት በበቂ ሁኔታና ጥራት አላት።ሰዩም ሙልዬ ከአገር ቤት ዲቪ ደርሶት በአሜሪካ ቆንስላ ጽ/ቤት (ኤምባሲ) የዲቪ ፕሮሰሱን እንደጨረሰ ከአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተነስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ አሜሪካን ሃገር አትላንታ ከተማ ሃርሰን ፊልድ ጃክሰን(Hartsfield-Jackson)አውሮፕላን ማረፊያ ደረሰ። ለመጀመሪያ ጊዜ አትላንታ ከተማ ለሚመጣ ሰው ከተማውን ከአየር ሆኖ ቁልቁል ለሚመለከታት ጥቅጥቅ ያሉ ዛፎቿ የአትላንታን ደን እንጂ ከተማ አያስመስሏትም።

ሰዩም አትላንታ እንደመጣ የተቀበለው ሰፖንሰሩ ሙሄ ድሮ በሱዳን ሃገር በኩል ወጥቶ አትላንታ ውስጥ 27 ዓመት ያስቆጠረ አጎቱ ነበር።ሙሄ ለ11 ዓመት ያልተለየቻውን Toyota Camry ይዞ ነበር የጠበቀው።ሰዩምና ሙሄ ተገናኝተው ወደ ቤት መንገድ እንደጀመሩ "እየሁልክ!" አለው ድንገት ሙሄ ሰዩምን "እዚህ ሃገር መጀመሪያ የማስጠንቅ አንድ ትልቅ ነገር አለ ቢኖር ምንም ዓይነት ወሬ ለሰው እንዳታወራ በ 5 ደቂቃ ውስጥ የከተማ ሰው እየተደዋወለ ከሁሉም ጆሮ ይደርሳል" አለው።ሰዩም ገና የናፍቆት ወሬውን ሳያወጣ ቤት ገብቶ የደከመ ጎኑን ሳያሳርፍ እንደ እዚህ ዓይነት መርዶ መስማቱ አስደንግጦታል አሳስቦታል።አሁንም ሙሄ ምክሩን ቀጠለ " ሰው የመሆን ህልም እና ሰው ያለመሆን ህልምህ የሚጀምረው አሁን ነው እዚህ ሃገር ሰው ልሁን ካልክ ትሆናለህ ልጥፋም ካልክ ትጠፋለክ ምን ያህል ይከፍሉኛል ሳይሆን ምን ያህል እቆጥባለሁ የሚለውን አባባል





ልብህ ውስጥ ፃፈው። ገንዘብ እንዳትንቅ ፣ገንዘብ እንዳታባክን አሁን በዲቪ የምትመጡ እድለኞች ናችሁ መንገድ የሚመራ ሁኔታውን የሚያስረዳችሁ እኛን አገኛችሁ በእኛ ጊዜ ሁሉም ጨለማ ነበር ሆኖም ሁሉንም ችግር ተቋቁመን ኑሮን መስርተን እየኖርን ነው። ሽንጣቸውን ገትረው የተማሩት አሁን ጥሩ ላይ ጥሩ ኑሮ ይኖራሉ በወዛደርነት የጀመሩ አሁንም ወዛደሮች ናቸው።እኔ ፓርኪንግ ነው የምሰራው ያኔ በእኛ ጊዜ ፓርኪንግ ላይ ስርቆት ነበር አንዳንዶች የሰርቁትን ጠጡበት ዘሞቁበት ገንዘቡን አጠፉት ዛሬ ላይ ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ ነው።እኔ ሰርቄ ባጠራቀምኳት ገንዘብ አንድ ነዳጅ ማደያ ገዝቼአለሁ አዲስ አበባ ላይ ያየህው የገዛሁትም ቤት በዚሁ ፓርኪንግ ላይ በሰበሰብኩት ገንዘብ ነው። የሚሰርቅበት ቦታ ከገባህ ሰረቅ የምትሰርቀውን ቁምነገር ላይ አውለው።ህይወትከን ለዘለቄታው ዋስትና ስጠክ ማለት ነው ዕውቀቱ ካለህ ተማር በቃ ከዚህ ውጪ እንደ አጎትነቴ የምመክርክ የለኝም አለው" ሰዩም በፅሞና ሲያዳምጠው ከቆየ በኋላ አግራሞት እና ፍርሃት የተቀላቀለበት ስሜት ተሰማው። እንዴት ዓይነት ነገር ነው አገር ቤት ሰው ሃብታም መሆን የሚችለው ሰርቆ ነው እዚህም የስርቆት ህይወት ታሪክ ተከትሎኝ ይምጣ፤ግን እኛ ሃይማኖተኞች ነን የምንል የውሸት ነው ማለት ነው እያለ በውስጡ እያሰበ እያለ "ቤት ደርሰናል" ሲለው ከገባበት ሃሳብ ነቃ።ሰዩም የአሜሪካ ሻውሩን፣ መጸዳጃ ቤቱን ፣ማብሰያ ምድጃዎችን እና መኝታ ቤቶቹን ወደዳቸው እየሰነባበተ ውችውንም ማየት ጀመረ ሁሉ ነገር አለ የሚበላው የሚጠጣው የሚለበሰው ነገር ሁሉም አግባብ ዋጋ ነው።የሚፈልገውን ነገር በቀላሉ በአቅራቢያው ያገኛል አሜሪካ ገባችሁ።

ውሎ አድሮ ሰዩም ሥራ ፈልጎ ከአንድ የነዳጅ ማደያ ተቀጠረ።የነዳጅ ማደያው ባለቤት ዕድሜ ወደ 65 ዓመት የሚጠጋ ህንድ ነበር።ስለ ስራው አጠር ያለ ማብራሪያ አደረገለት "ከአንተ በፊት የነበረውን ልጅ ያባረርነው እየሰረቀ አስቸግሮን ነው ስለዚህም አንተም በተቻለ መጠን በሃቅ ለመስራት ሞክር!ገንዘብ ሊዘርፍ ዘራፊ ቢመጣብህ እንዳትከራከር የሚፈልገውን ይውሰድ መጀመርያ ህይወትን ከአደጋ መጠበቅ ነው ያለብህ" እያለ አጠር ያለ ማብራሪያ አደረገለት።ስራውን እስክትለምደው ድረስ እንዳንተ ኢትዮጵያውት የሆነች ሊዲያ የምትባል የጠዋት ፈረቃ ሰራተኛ ታስለጥንሃለች እሷም አሁን ትመጣለች" ብሎ ከሊዲያ ጋር አገናኝቶት ህንዱ ወጥቶ ሄደ።

ሊዲያም በተሰጣት ትዕዛዝ መሰረት ሰዩምን ማሰልጠን ጀመረች "አይዞ ሁሉም ነገር ይለመዳል አሜሪካን አገር ጥሩ ነው አሜሪካኖች ሰርቶ አደርን ይወዳሉ የቋንቋ ችግር አያስጨንቅህ እነሱ እንደምንም በምልክት ያስረዱካል ዛሬ የፈራከው ቋንቋ ነገ እየቀለድክ ትሰራበታለክ ይሄንን አገር አወደዋለሁ ጥገኛ አትሆንም የራስክን ስራ ሰርተክ በራስህ ዛቢያ እየተሽከረከርክ መኖር ትችላለህ።ለእኔ ምቹ ነው ችግሩ የእኛ ህዝብ ከዚህ ከመጣ በኋላ ኋላቀር አስተሳሰቡን ትቶ አውልቆ መጣል ይሣነዋል እንደ ሃገርኛ ሆኖ መኖር ይፈልጋል አንድ

አካባቢ ሆኖ መርመጥመጡ ያስደስተዋል እኔ እንኳን ሃበሻ ሰፈር አልኖርም ነጮች አካባቢ ነው የምኖረው ስለ እኔ የሚያወራ የሚጨነቅ ሰው የለም እሉሽ እሉሽ! አልሰማም አዲስ እንደመጣሁ ጨርቄን ጥዬ ላብድ ነበር" "በዲቪ ነው የመጣሽው?" አላት ሰዩም በወሬዋ መሃል ገብቶ "አይ አይደለም ባል ነው ያመጣኝ አዎ ያመጣኝ ባል ነው በዕድሜ፣በትምህርት ደረጃ፣በአስተዳደግ እንለያያለን በፍፁም የሁለት ዓለም ሰዎች ነን አሜሪካን ሃገር ለመምጣት ስል ነው ያገባሁት በእርግጥ ተሳክቶልኝ መውጫ አድረጌዋለሁ ወረቀቴን እስካገኝ እና አገሩን እስከለምደው የግድ አብሬው መቆየት ነበረብኝ እናም ለአንድ ዓመት አብሬው ቆየሁ አንዱን ዓመት በአስር እባዛው ሲኦል ውስጥ ነበር የነበርኩት ማለት እችላለሁ።ቤት ውስጥ አስገብቶ በገባ በወጣ ቁጥር ልውጣብሽ ነው የሚለው ከሰው ጋር እንድተዋወቅ ስራ እንድሰራ አይፈልግም በዛ ላይ ሴት ልጅ መንከባከብ አይችልም በራሱ ፍላጎት እና ስሜት የሚጓዝ ሰው ነበር ወጥ እየቀቀልኩ ቤት እያስተካከልኩ ልብስ እያጠብኩ እንድኖር ነበር የሚፈልገው ብቻ ግን ብለን ብለን በመጨረሻም ልጅ ውለጂ አልወልድም አታካራ ጭቅጭቅ ወደ ለየለት ጥል አምርቶ መጨረሻ ቤቱን ለቅቄ ወጥቼ ሥራዬን እና ሰላሜን ጀምሬ አሁን ድረስ አለሁ።አገር ቤት ቤተሰቦቼን እረዳለሁ  እኔም እዚህ ጥሩ ቤት ውስጥ እኖራለሁ ጥሩ መኪና እነዳለሁ ከፈለኩበት ቦታ ወጥቼ ባድር የሚቆጣጠረኝ የለም ህይወቴ ደስተኛ ነች።" "እንደ ገና አላገባሽም ማለት ነው?"አላት ሰዩም "አይ አንተ ማግባት ከባድ ነው እየህ ባል እኔን ሲያገባ ስጋዬን ብቻ ሳይሆን ነብሴንም፣ፍላጎቴንም፣ማንነቴንና ስሜቴን አብሮ ማግባት አለበት መግባባት መቻቻል አለብክ መግባባት ማለት ደግሞ የምፈልገውን የሚያውቅ፣ ለሴት ልጅ ክብር የሚሰጥ፣ ከገንዘብ በላይ እኔን የሚወድ እና  ፍላጎቴን የሚያሟላ መሆን አለበት።አገር ቤት እናቶቻችን አይተህ ከሆነ የባሎች ጥገኛ ሆነው ስለሚኖሩ ዘለፋና ችግርን ችለው አብረው ይኖራሉ እነሱ አቅም ከፈቀደላቸው ውጭ ከፈለጓት ሴት ጋር ይቀብጣሉ ቤት ገብተው የሚሰቶቻቸውን ሰላም ይነሳሉ ይሄን ሲያ ያደገ ወንድ ልጅ እዚህም ቢሆን ሴትን ልጅ እንደ አባቱ አድርጎ መያዝ ይፈልጋል እኛ ሴቶች ደግሞ የእናቶቻችን ሁኔታ ስለሚዘገንነን ያንን ዓይነት ህይወት መድገም አንፈልግም በቃ '[GOD BLESS AMERICA]' አንተ አሁን መጀመሪያ ማድረግ ያለብህ የአገር ቤት አስተሳሰብን አመለካከትህን ከአገር ቤቱ ልብስ ጋር አውልቀህ ጣለው ቆንጆ ቤት ውስጥ ኑር ቆንጆ መኪና ንዳ ራስህን ተንከባከብ ጥሩ ጥሩ አልባሳትን ልበስ ለራስህ ደስታ ፈጠረክ ማለት ነው ከዛ ሌሎች የምትፈልጋቸውን ነገሮች በሂደት ታገኛቸዋለህ አይዞህ አትላንታ ቆንጆ አገር ነች ከዲሲ ቀጥሎ ብዙ ሃበሾች እንደሚኖሩባት የሚነገርላት አትላንታ ብዙ ቤተክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ ምግብ ቤቶች፣ ሺሻ ቤቶች፣ ጭፍራ ቤቶች እና ሬዲዮ ጣቢያዎች ያሏት ሃበሻ ሃበሻ የምትሸት ከተማ ነች። እዚህ ሃገር ትንሽ የሚከብደው ማን ጋር ጓደኛ መሆን እንዳለብክ ሰውን ለይቶ ማወቅ ላይ ነው እኔ እንደታዘብኩት ብዙ ሰዎች ሰርተህ ስትለወጥ ይቀኑብሃል የምታደርገውን ነገር በአጠቃላይ እያንዳንዷን ነገር ስለአንተ ማወቅ ይፈልጋሉ ራስህን ዝቅ ስታደርግላቸው እንደ





ሞኝ አይተው ሊንቁህ ሊያዋርዱህ ይሞክራሉ ብልጥ ስትሆን ቅፅል ስም ይሰጡካል ይታከካሉ በራሳቸው ፍላጎት ሳይሆን ባንተ ፍላጎትና ምርጫ የሚኖሩ ናቸው አንተ የገዛሃውን ዓይነት መኪና መግዛት ይፈልጋሉ አንተ ቤት ብትገዛ አንተ ቤት ስለገዛህ ብቻ ሳያስቡት ዘለው ቤት ይገዛሉ አንተ ምክንያታዊ ሆነህ የወደድካትን ልጅ ጓደኛህ ያለምክንያት ይወዳታል፣አንተ አቅም በፈቀደው ሠርግ ብትሰርግ ጓደኛክም ይሰርጋል ምን አለፋህ ተከትሎን የመጣው የፉክክር፣የመጠላለፍ፣የመቀናናትና የመጠፋፋት ባህል ሃበሻውን ዕርስ በዕርስ ሲያባላው ይኖራል ወጣ ብለህ ስለ ሃበሻው ስትሰማ ሮሮ አቤቱታ ነው የምትሰማው የራሴ ጓደኛ እንዲህ አደረገኝ የራሴ ዘመድ እንዲህ ሰራችኝ እንዲሁ አንድ ላይ ሲርመጠመጥ ሲበሻሽቅ ነው የሚኖረው የሚገርመው ደግሞ ተለያይተው መኖር አይችሉም አንድ ላይ መኖር አይችሉም እውነቴን ነው የምልህ ብዙ ሰው ስታገኝ ስትደሰት መደሰትን ሳይሆን ስትወድቅ ስትቸገር ማየት ያስደስታቸዋል በውድቀት በችግር ጀርባ ይሳለቁብሃል ሲኖርህ ስትበልጣቸው ይጠሉካል እረ ተወኝ ወንድሜ ከባሌም ከሃበሻም በደህና ቀን ነው ርቄ የሄደኩት።ደግሞ ይሄውልህ ሰዩም እዚህ ሃገር ከሴቱ ይልቁ ወርኛው ሆነ አሉባልታ ያስቸገር ወንዱ ነው አደራ ከወረኛ ወንዶች ጋር ጓደኝነት እንዳትጀምር የማያወሩት ነገር የለም አሁን እኔ እዚህ እየሰራሁ ነው አይደል የዚህ ባለቤት ደግሞ ይሄ ህንድ ነው በእነሱ እይታ እኔ የህንዱ ውሽማ ነኝ ሰርተን መኖር እንኳን አልቻልንም ማታ ላይ ከአንተ ጋር ቢያዩኝ ይሄን ደግሞ ያዘችው ነው የሚሉት ምረጡ ብለህ ገንዘብ እና ወሬ ብታቀርብላቸው ወሬን ነው ቆንጥረው የሚሄዱት በዛ ላይ ሴሰኛው እና ሰካራሙ እየበዛ ነው በተቻለ መጠን ራስከን መጠበቅ አለብህ ስትዝናና በመጠኑ ሰው ስትቀርብ በመጠኑ " 'By the way' እኔ ስትጠራኝ ሊዲያ ሳይሆን ሊሊ ብለህ ነው"ብዙዎች ሊሊ ብለው ነው የሚጠሩኝ እሺ" አለችው ፈገግ ብላ። ሰዩም በሊዲያ ወሬ ተመሰጠ ትክክለኛ እህታዊ ምክር እንደመከረችው ገብቶታል ሊዲያ ገራገርና በስራዋ ቀልጣፋ ናት "አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ አላት ድንገት ሰዩም ?"  "ምን ነበር አለችው ውብ ጥርሶቿን ፈልቀቅ እያደረገች?"

"መቼ ነው የምታገቢው?መቼ ነው የምትወልጂው? ዕድሜና ቁንጅና እኮ ቁሞ አይጠብቅም.....!" አላት እርግጥም እውነት ነው ሊዲያ አሁን ያላገባች አሁን ያልወለደች መቾ?ዕድሜዋ ሰላሳዎቹ መባቻ ገብቷል መካከለኛ ቁመት እና ደልደል ያለ ሰውነት ያላት ሊዲያ ዓይነ መልካም ጸጉሯ ረጅም ሥስ ከናፍርት እና ችምችም ያሉ ጥርሶች አሏት ሊዲያ በዚህ ዕድሜየዋ ቤተሰብ ካልመሰረተች በቆየች ቁጥር ነገሮች እየከበዱ እንደሚሄዱ ገሀዳዊ እውነት ነው።

"...............ይሄውልህ ሰዩም ቅድም ነግሬካለሁ እኳ ዘንግተከው ካልሆነ እኔ ማግባት እና መውለድ ስላለብኝ ብቻ የማልፈልገውን አግብቼ የማልፈልገውን ልጅ አልወልድም!ልጅ እወልዳለሁ ብዬ እኔ መሞት አልፈልግም ጊዜው ሲደርስ እኔ የምፈልገውን ዓይነት ሰው

ሳገኘው ያኔ አገባለሁ እለበለዚያ ግን ከራስ ጋር መኖርም ትልቅ ፀጋ ነው"አለችሁ ሊዲያ ስዩም ገረምው ከቁንጅናዋ ይልቅ የአቋም ውሳኔዋ ከማስደነቅ አልፎ እያስቀናው።

ስዩም ሃገሩ ለመደ ከሰዎች ጋር ተላመደ ስራውን ለመደ ስርቆትም ተለማመደ መሸታ ቤቶቹንም ማካለል ጀመረ።ጆሲ፣ዘሌ እና ቴዲ የሚባሉ ጓደኞች አፈራ ሁሌም አርብ እና ቅዳሜ ማታ በሃበሻ ጭፈራ ቤት እነ ዘሌ ጠርሙስ ውስኪ እያወረዱ መዝናናትን እየተለመደ መጣ ከብዙሃን ዓይንም እየገቡ መጡ ባለጠግነታቸውም ከተቀጣሪ የጋዝ ስቴሽን ሰራተኝነት እንደሆነም ሁሉም ጠንቅቆ ያውቃል እንዳንዴም ወጣ እያሉ *ለለ፤ ፋሪሷ* መቀማመስ ጀመሩ ይሄን ስዩም የነበረበትን ዓለም እስተዳደጉን ሁሉን ነገር ረስቶ ጭልጥ ብሎ ወደ ዘመናዊናት ገባ ስሙንም ሲሲ በሉኝ አለ ስዩም ቀርቶ በሲሲ መጠራት ጀመረ ሲሲን ልጃገረዶችም ያሳዱት ጀመር ሲሲ ሲጋብዝ ዓይነ ሙሉ ነው መታየት መደነቅ ያስደስተዋል ከሚከታተሉት ብዙሃን ኮረዳዎች እንዷ ፍሬህይወትን(ፈፊን) ጠበሰ ስዩም ይበልጥ ገነት ገባ ቀጭን ወገብ እና ወፈር ያለ ዳሌ ያላት እግሮቿ ረዘም ብሎ ጭኖቿ በጥንቃቄ የተንበለበሉ የሚመስሉ አጭር ነገር የምታዘውትረ ፍሬህትወት ስዩም 6ኛ ጓደኛዋ መሆኑ ነው፡፡

ፍሬህይወት ጥራ ግራ ማደር አትፈልግም ምንጊዜም ቢሆን በውበቷ ትመካለች የፈለገችውን ነገር ማንንም አማላ ማግኘት እንድምትችል ታውቃለች ያሳለፈቻቸው 6ቱ ጓደኞቿ አንዱ መኪና አንዱ ቤት አንዱ ጥሬ ገንዘብ በአጠቃላይ ሁሉም ኢንቨስት አድረገውባታል.....................።ፍሬህይወት ላንቺ በዬ ነው እንቺን አፍቅሬ ነው የሚሏትን ጅል ወንዶች ትንቃቸዋለች ለእሷ ብለው ሳይሆን ሴሰኝነታቸው እያቅበዘበዛቸው የእሷን ውብ ገላ ፍለጋ እንደሚመጡ ታውቃለች።

አሁን ሲሲ ለፈፊ ተረኛ ነው የፈለገችሁን ሁሉ ያደርጋል ሲሲም ከእሷ ጋር መሆን የእሷ ተብሎ መጠራቱ ራሱን ከሰው ሁሉ የተለየ እንድሆነ አድርጎ ቀናቶች ወራቶች አመቶች ተቆጠሩ ሲሲ ያሳለፈውን ዘወር ብሎ ሲያስተውል ቢታመም እንኳን አንድ መዳሃኒት የሚገዛበት በቂ ገንዘብ በባንኩ አለመኖሩን ሲያስብ ከነከነው አገር ቤት ጥሎቸው የመጣው ጓደኞቹ እንኳን እዛው በሃገራቸው ተምረው ህይወታቸው ቀይረው የሰከነ ኑሮ እየኖሩ እንደሆነ ይሰማዋል አንድ ቀን ፈፊ ላናግርሽ እፈልጋለሁ አላትና የሰከነ ህይወት መኖር እንዳለባቸው ልጅ መውለድ እና ማሳደግ እንዳለባቸው አስረዳት ፈፊ ጊዜ አላጠፋችም እኔ እና አንተ አንተዋወቅም ይሄው ብትደውል እኔን ለመረበሽ ብትሞክር 911 ደውዬ ኑሮህን እስርቤት ነው የማደርገው እኳ እኔ ካንተ ወልጄ ያንተን ልጅ ሸንት ልጠረግ የማነህ ደፋር ባክህ ብላ እርሙን አውጥታለት ባለበት ጎሊታው ሄደች።

የስዩም ጓደኞች ይህንን በሰሙ ጊዜ ለመለያየታቸው ደስታ ፅዋ አንስተው ሲጠጡ አደሩ ስዩም በሌለበት እነ ዘሌ ሲያዝናኗት አደሩ እግረ መንገዳቸውንም ፈፊ ከስዮም





ወደ ዘሌ ተሸጋግራ የጥንዶሽ ርክክብ አደረጉ።ስዩም ብቸኝነት አበዛ ሁሉ ነገር አስጠላው የፈፊን ገላ ለምዷል ከዛ ገላ ርቆ መኖር አንገሸገሸው በቃ ወሰን ያለ እሷ ከመኖር ራሱን እየጎዳ ከእሷ ጋር መኖር መረጥ ለጓደኞቹ ደወለላቸው ማታ ላይ ሊያገኛቸው እንደሚፈልግ እና ከፈፊ ጋር እንዲያስታርቁት ተማፀናቸው እነሱም ምንም ችግር የለም አሉት ቀኑ መሸ ማታ ላይ ተገናኙ ወሬው ተጀመረ ዘሌ እና ቴዲ ሲሲን አይዞ እያሉ ያጽናኑትታል በዚህ መሃል ፈፊ ድንገት ወዳሉበት መጣች ዘሌም ቆሞ በእቅፍ ውስጥ አስገባት እና ከንፈር ለከንፈር ተሳሳሙ መጠጥችሁ መጠጣት ስዩም ያየሁን ማመን አልቻለም ወድ አሜሪካ የመጣበትን ቀን ብቻ ሳይሆን የተወለደበትን ቀንም ረገመ ሁሉም ነገር አብቅቷል ስዩም ከፍሬህይወትም ከገውደኞቹም ከገንዘቡም ከዘመጀችሁም አልሆነም ድንገት ተፈትልኳ ወጣ መኪና ውስጥ ገብቶ ሳግ እየተናነቀው እስኪበቃው አነባ አለቀሰ ግና ያን ሁሉ ስህተት በዚች ለቅሶ መመለስ ከቶውንም ቢሆን አይቻልም ብቻውን ሌላ መጠጥ ቤት ገብቶ እየጮሀ ሲጠጣ አደረ ሰከረ ወድ ቤቱ ለመሄድ መኪና አስነስቶ ሲሄድ ድነገት መንገድ ላይ ፖሊስ አስቆመው ጠጥቷል የስዩም ዕጣ ፈንታ ወደ እስር ቤት ነበር እስር ቤት ገብቶ ቅጣቱን ጨርሶ ወጣ መንጃ ፍቃዱን ተቀማ በብስጭት ስራውንም አቆመ ።ስዩም ያሁሉ አልፎ መጨረሻ ላይ ሁሉን ነገር አጥቶ ከመኖሪያ ቤቱ ወጥቶ ጎዳና ላይ ኑሮውን አደረገ።

## *" ስታር ባክስ "*

ቀኑ ቅዳሜ ከሰዓት ወደ ማታ ገደማ....ሙቆ የዋለው አየር እየቀዘቀዘ መጥቷል....እሽሽሽሽ ...እያለ ረጅም ፀጉርና ቀሚስ የሚያውለበልብ ደስ የሚል ንፋስ ይነፍሳል....*ላቪስታ* መንገድ ላይ ካለው ስታር ባክስ ካፌ በረንዳ ላይ ከወትሮው በተለየ ሰው በብዛት ተልከሰከሷል....ብዙሃኑ ሃበሻ ነው....አሜሪካን አገር በየትኛውም አበሻ የሚኖርበት ከተማ ስታር ባክስ ካፌ ላይ የሃበሻ መብዛት የተለመደ ነው። ሊዲያ ቅዳሜ...ቅዳሜ...በዚህ ሰዓት ከጓደኛዋ ኤደን ጋር እዚህ ላቪስታ ስታር ባክስ ይገናኛሉ። ሊዲያ ረጅም ፀጉሯን በደረቁ ብትንትን አድርጋ ነፃ ሊቃዋለች....ፀጉሯም በነፃነት ከነፋሱ ጋር ይጫወታል....ብሊውሊውሊው ....እያለ ይርገፈገፍና እንደገና የራሷን ጉንጭ ያጣፍናታል....አይኗን መጥቶ ይሸፍናታል......ዘወር በል ብላ በእጇ ትመልሰዋለች እንደገና ተንደርድሮ ይመለስና አይኗን ይሸፍነዋል....ንፋሱ ፀጉሯን ሲያጫውት ይቆይና ወረድ ብሎ በነጩ ላይ በጥቋቁር ነጠብጣብ ያሸበረቁ አጭር ቀሚሷን ለመግለብ ይታገላታል.....በሩን ከፍታ ገባች ። ከፊት ለፊቷ ወደ አምስት ሰዎች ረድፍ ተራ ይዘው ቆመዋል....ስድስተኛ ሆና ወደ ፊት ስትንፏቀቅ ቆየችና ወረፋዋ ሲደርስ አንድ መካከለኛ ኩባያ ላቴ ብላ አዘዘችና ሂሳቧን ከፍላ ተመልሳ በረንዳ ላይ ወደ ተደረደሩ ወንበርና ጠረጴዛዎች ነፃ ቦታ ፈልጋ ተቀመጠች። ንፋሱ ይበልጥ እያማረ መጧል....ቀዝቃዛውን አየር ዘግኖ እና ቀዝፎ ....ሹሹሹሹሹ....ብሎ ለሰው አቀብሎ ፁጥ ይላል....ይመላለሳል.......................

ጭው..ጭው....ጭው...ቷ.....በአእዋፍ ዜማ ቅጅ የሚጠራው የሊዲያ ስልክ ፖርሳዋ ውስጥ እየተንጨረጨረ ዘመረ....ፖርሳዋን ከፍታ እስከምታወጣው ድረስ ጊዜ አልሰጥ አላት....እንደ ተራበ ሕፃን ልጅ አጣደፋት....። በፍጥነት አውጥታ የተደወለውን ቁጥር አየች። ጓደኛዋ ኤደን ነች.....የት ነሽ ...አለቻት ..ኤደን... ከተለመደው ቦታ ብላ መለሰችላት። መጣሁ ብላ ኤደን ስልኩን ዘግታ ከስምንት ደቂቃ በኋላ ደረሰች....መኪናዋን አቁማ በቀጥታ ወደ ስታርባክሱ በረንዳ በፍጥነት ራመድ ራመድ እያለች ተራመደች.....ሊዲያ ላይ የቀለደው ንፋስ ኤደን ላይ መቀለድ አልቻለም....ኤደን ጥብቅ ያለ ጅንስ ከላይ ጥብቅ ባለ ካኔትራ ለብሳለች...ፀጉሯን ሽምጥጥ አድርጋ ለኋሎሽ ጠፍራ አስራዋለች....ንፋሱ የሚገልበው....የሚያውለበልበው ቢያጣ ጆሮዋ ላይ አፏጭቶ ይሮጣል.....

ኤደን እና ሊዲያ ተቃቅፈው ሰለምታ ከተቀያየሩ በኋላ...ምን ያዝሽ አለቻት ኤደን....ላቴ አለቻት ሊዲያ...እኔ እንኳን ግሪን ቲ ልያዝ መሰል...እሱ ሳይሻለኝ አይቀርም...ሰሞኑን ዳይት ላይ ነኝ አለችና ኤደን ገብታ ግሪን ቲ ይዛ ከሊዲያ አጠገብ ወንበር ስባተቀመጠች።

እንዴት ነሽ ባክሽ አለች ኤደን....ድክም ብሎች ነው ያደርኩት ....ትላንት ብዙ ፔፐር ወርክ ነው የሰራሁት አለች ኤደን።...ኤደን ለእናት እና ለአባቷ ሁለተኛ ልጅ ነች..,አንድ ታላቅ ወንድሟ እና እሷ ብቻ ናቸው...አባቷ አስተምሯቸዋል...በግብረ ገብ አዳብሯቸዋል...በፕላን መኖርና በዘፈቀደ መኖር የአንድን ሰው የሃብታምነት እና የድህነት ዕጣ ፋንታ መወሰኛ መሆኑን እየነገረ አሳድጓቸዋል። ዘፈቀደዎች የልጅ ሃብታሞች ናቸው....የልጅ ብዛት ደግሞ እንደ እግዜር ድንቅ ፀጋ በረከት አድርገው ይወስዱታል...በዚህ ጊዜ ልጆች ተዝረከርከው ያድጋሉ....በመጨረሻም ጥቂቶች ወጥተው ብዙዎች ይወድቃሉ....ተሳከቶላቸው ቁም ነገር ላይ ቢደርሱ እንኳ...ኃላፊነታቸውን በደንብ አይወጡም....ጉቦኛ...ሌሰኛ...ሱሰኛ...ቀናተኛ...ይሆናሉ...ሲወዱ ራሳቸውን ይገላሉ...ሲጠሉ ደግሞ ይገላሉ....ልጅነታቸውን እና ጉርምስናቸውን በወጉ ስለማያሳልፉ ....ሲጎለምሱ እንደ ልጅ ያደርጋቸዋል....እርጅና ሲመጣ ደግሞ ይጎረምሱና እድሜያቸው የማይፈቅደውን ነገር ያደርጋሉ....ይህ ሁሉ የድህነት ቁርፋት ነው....እያለ ነበር የኤደን አባት ልጆቹን ያሳደጋቸው። ኤደን ጥሩ ዩኒቨርስቲ ተመርቃ ዛሬ በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ወፈር ያላ ደሞዝ ይከፈላታል። ያባቷ ውጤት።

ኤደን አላገባችም። ሊዲያም ያባቷ እድሜ የሆነው ባሏ ጋር ከተለያየች ወዲህ ጋብቻ አልሞከረችም። ሁለቱም ተመሳሳይ እድሜ ላይ ናቸው። ሰላሳዎቹ መባቻ። እኔ ምልሽ አለች ሊዲያ....እዛ ልጅ ጋር ያኔ ቁጥር ተቀያይራችሁ ነበር ....ምን ላይ ደረሳችሁ ...ብላ ጠየቀቻት

እ...አለች ኤደን መጀመሪያ ግራ እንደተጋባች ሁሉ...ግሪን ቲዋን አንስታ ፉት ብላ መልሳ እያስቀመጠች...አልሆነም ባክሽ። አለቻት ቁርጥ ባለ ትንፋሽ።.....እንዴት አለች ሊዲያ... ቀጠለችና....ይሄ ሰው መናቅ ይቅርብሽ...ማለቴ..አለች...ሊዲያ እያቅማማች...በሶፍት





ከንፈሮቿን ዳበስ ዳበስ እያደረገች....አንቺ ጥሩ ቤተሰብ ያለሽ...የተማርሽ....ትልቅ ደሞዝ ያለሽ....እኔ አንቺን ልምከር እንዴ....እኔ እንኳ ጋዝ ስቴሽን ቁሜ እየዋልኩ...አቁሞ ሚያሳድር ባል እየፈለኩ ነው...አለች ፈገግ ብላ..ሊዲያ.... ምን መሰለሽ ሊሊ....አለች ኤደን...ድሃ ነው....የአስተሳሰብ ድሃ...የአስተዳደግ ድሃ....በስሜቱ ብቻ የሚሸመጥጥ....ፈገግታን እንደ ፍላጎት ወስዶ....ገና ምንንም ሳንተዋወቅ ከበላየ ላይ ሊሳፈርብኝ አማረው....እውነቴን ነው ምልሽ ሊሊየ....ከባድ ነው...የሰው ፀባይ አስቸጋሪ ነው...ያልሆኑትን ይሆናሉ....የሌላቸውን አለን ይላሉ...ሳይማሩ ምሁራን ናቸው.....የሆነ የማይገባኝ መካከል ላይ የጎበጠ ነገር ይታየኛል....ሰው መጀመሪያ ነገር ራሱን ሆኖ አይተዋወቅም.....ማንነት መቅደም አለበት...በወሬ እንዲህ ነኝ ከማለት...ራስን በተግባር መግለፅ የመልለ ምስክርነት የለም....ኑሯችን መካከል ላይ ጎብጧል....መቃናት አለበት...ሚያቃናው ቁርጠኛ ሰው ያስፈልገዋል...የድሮ ትውልድ አይተሽ ከሆነ የራሳቸው ምህዳር ነበራቸው...እያቶቻችን በጦርነት...በወራሪ ወቅት....ፋከራን...ሽለላን..ፈጥረው ተዋግተው መከቱ.....አገር ይዘው...አገር ...ወግ...ባህል....ቋንቋ...እምነት አስረከበውን ሄዱ። እኛ ያሁኖቹ ደግሞ....በእምነታችን ላይ ራሳችን ስንፈላሰፍ ከእምነታችን እየወጣን ነው....ባህላችን በረዝነው....ቋንቋችን ተጠየፍነው....እዚህ ካሉት ውስጥ አንዱን ...ደህና ዋልክ ብትይው...ዋትስ አፕ ነው የሚልሽ.....እና ሊሊየ...በአሁኑ ጊዜ ሲሪየስ የሆነ ሪሌሽን የለም....ገላ ሻጭ እና ገላ ገዥ ነው ያለው....እኔ በበኩሌ ምንም የሚያጣድፈኝ ነገር የለም....ይልቁንስ ቤት እቀይራለሁ ብለሽብ ነበር ቤቱን አገኘሽ...አለቻት ኤደን የወሬውን ርዕስ ለመቀየር እንደፈለገች ሁሉ..... ድንገት ከፊታቸው አንድ የቆሸሹ ልብሶች የለበሰ ...የሽታው ጠረን አፍንጫን የሚከነክን...ሰው....ሆምለስ...ብሎ...የልመና እጁን ወደፊት ዘረጋ.....ኤደን ይበልጥ እንዳይቀርባቸው እየተጠነቀቀች.....በፍጥነት ከፖርሳዋ ሦስት ዶላር አውጥታ ሰጠችው....አመሰግናለሁ። አለ በአማርኛ። ...እንዴ ሃበሻ ነህ ...አሉት ...ኤደን እና ሊዲያ ...እኩል ባንድነት.....አወ ብሎ ፈገግ አለ ....ሆምለሱ.....ድንገት ደንገጥ አለች ሊዲያ...ይሄን መልክ ታውቀዋለች.....ጭንቅላቷ ጊዜ አልወሰደም...አስታወሰችው....እንዴ....ስዩም...ብላ በድንጋጤ ጮኸች።

# የስለት ልጅ

ማንኛውንም ስራ ስትሰራ ማንጎራጎር ትወዳለች ሁሌም ደስተኛ ነች ሃብታም አይደለችም ለዕለት ጉርሷና ለዓመት ልብሷ ብቻ የሚሆን ካገኘች ትርፍ ገንዘብ አትፈልግም ትርፍ ገንዘብ ብታገኝ እንኳን ለቤተክርስቲያን ጧፍ ለተቸገሩ ምግብ ይዛ ትሄዳለች ይሄ ነው የሚባል ወጥ ስራ የላትም እንጨት ለቅማ ትሸጣለች ጥጥ ትፈትላለች ሲበዛ ደግ ሰው ናት የተቸገረ የታመመ ካየች እንባ ከዓይኗ ያለማቆም ይወርዳል ሰው ሲታብ ከምታይ እሷ ብትራብ ትመርጣለች አቻሽ ተወልዳ ያደገች አይምባ ከምትባል ትንሽ የገጠር መንደር ውስጥ ነበር ወላጆቿ ዕድሜየዋ ለአቅመ ሄዋን ሳይደረስ ገና በጮርቃ ዕድሜ ባል አጋብተዋት ከአቅሟ በላይ ሲሆን በ13 ዓመቷ ነበር ወድ ጎንደር ከተማ ጠፍታ የመጣችሁ።አቻሽ አሁን ዕድሜዋ ወድ 48 አካባቢ ትሆናለች።ጎንደር ከተማ እንደመጣች ለ11 ዓመት በሰው ቤት በሰራተኝነት ተቀጥራ ትሰራ ነበር በኋላ ላይ ግን አንዲት የቀበሌ ቤት አግኝታ ኑሮዋን በዛች ቤት የግል ስራዋን እየሰራች መኖር ጀመረች በሰፈሩ እየዞረች እንጀራ ትጋግራለች፣ልብስ ታጥባለች በአካባቢው ሰው ተወዳጃ ናት።

አቻሽን የአካባቢው ልጆች ላዬ እያሉ ይጠሯታል ለቅሶ ካየች ከሃዘንተኛው ይልቅ ሙሾ እየደረደረች አምርራ በማልቀስ ትታወቃለች በዚህ ምክንያት ደግሞ እናቷን ሳታያት እንደወጣች ስለሞተችባት የእናቷ ሃዘን ሆዷ ውስጥ ዘላለማዊ ስለሆነባት ነው። የአቻሽ የሕይወት ታሪክ አሳዛኝነቱ ይበዛዋል።እናቷ ቀንጆ እንደነበረች ትናገራለች ታዲያ እናቷ በአፍላ ዕድሜዋ ባል አግብታ ኑሮ ስትጀምር በሌሊት ሶስት ሰዎች ቤቱን ከፍተው በመግባት ባልየውን ገለው እናቷን አስገድድው ከደፈሩ በኋላ የባሏን አስከሬን ሰውረው እናቷን የደፈራት የእናቷ ባል ሆኖ እንደቀረና እሷም ከነብስ ግድያው በኋላ አስገድዶ መደፈሩ ላይ መረገዟን ትናገራለች።አባቷን አትወደውም ነፍስ ገዳይ ነው!አቻሽ እንደ አባት የምታስበው እና በስሙ የምትጠራው በግፍ በተገደለው በእናቷ የህግ ባል ስም ነው።ብዙን ጊዜም የሚያስለቅሳትም በእናቷ አለመታደል እና ያንን ሁሉ ግፍ ተቀባይ መሆኗ በአንጻሩ ደግሞ ይህ ነብሰ ገዳይ በሰውም በእግዚሃብሄርም ሳይዳኝ ህሊናውም ሳይወቅሰው በሰው ጭቆና ቀንበር ስር ኑራ መሞቷ ነው።ከዕለታት አንድ ቀን ጎበዜ የሚባል ሰውዬ ከሩቅ ሃገር ለጸበል መጥቼ ነው እያለ በእነ አቻ ሰፈር ቁራሽ ይለምናል አቻሽም እንጀቷ አይችልም እና ግባ ብላ ቤት ያፈራውን አቅርባለት ከአሁን በኋላ ከጸበል መልስ ወደ እሷ ቤት መምጣት እንደሚችል ማደሪያ ከሌለውም ከእሷ ቤት እንዲያድር ፈቀደችለት።

አቻሽ ባልም ልጅም የለትም ቢሆንም ግን ጎበዜን ከልብ ስብዕና ልትረዳው እንጂ ለባልነት አስባው አይደለም።ሆኖም ግን ጎበዜ ከእሷ ቤት እየዋለ ሲይድር ከበሽታውም ሲያገግም ውሎ አድሮ የፍቅር ጥያቄ አቀረበላት አቻሽም ጊዜ አላጠፋችም





ፈጣሪ ለእኔ ይሆናል በሽታህን ሰበብ አድርጎ ከቤቴ የጣለህ ብላ የፍቅር ጥያቄውን ተቀብላ አብራው መኖር ጀመሩ።

አቻሽ ጎበዜን በማግኘቷ ደስተኛ ብትሆንም ልጅ ግን እምቢ አላት በምታገኛት በቆሎም ይሁን በዳቦ የምትዘከራትን ማርያም ጠዋት ማታ እየሄደች መማፀን ጀመረ። "እመቤቴ ሆይ ለልጅ አብቂኝ ስለቴንም አስገባለሁ የወለድኩ እንደሆነ በወለድኩ በ10ኛ ቀኔ ጥልሽን ይገፎ እገባለለሁ" ብላ ተሳለች።የአቻሽ ስለት ተሳክቶ ወንድ ልጅ አርግዛ ወለደች ስሙንም ሰጠኝ አለችሁ 'ሰጠኝ ጎበዜ'

አቻሽ በወለደች በ10ኛ ቀኗ ስለቷን አስገባች ስለቷን ባስገባች ማግስት ደግሞ ጎበዜ ቤቱን እና ሃገሩን ጥሎ ጠፋ።ምንም እንኳን አቻሽ ብቿን ብትቀርም የሰፈር ሰው ስለሚወዳት ልጁ በሰፈር ሰው እርዳታ አደገ እናቱ ጥሩ ሰው ስለሆነች ልጇን ሁሉም ይወደዋል ልብስና ጫማ የማይገዛለት የለም አለባበሱ እና የሰውነቱ ውፍረትና ጥራት የደሃ ልጅ አይመስልም ............ሰጠኝ አደገ ት/ቤት ገባ አቻሽም የምታገኘውን ሁሉ ለሰጠኝ ትሰጠዋላች የእናቷን ሃዘን እረሳች ሁሉም ነገር ለሰጠኝ ሆነ።

ሰጠኝ በሰፈር ሰው ተንቀባሮ አደገ ተንቀባሮ ተምሮ ዩንቨርስቲ በመግባት በአመርቂ ውጤት ተመርቆ የከተማዋ ከንቲባ አስተዳደር ሆኖ ሰውም ለዚህ ቁምነገር በመብቃቱ እና አቻሽ ለዚህ በመብቃቷ ደስተኛ ሆነ።ሆኖም ግን አቻሽ የሰጠኝን ፍሬ ሳትቀምስ ድንገት ታማ ይቺን ዓለም ተሰናበተቻት ሰው ወፉ እንስሳው ሁሉ አልቀሰላት ተንጫጫላት ሰጠኝ እናቱን ከቀበረ በኋላ በሰፈሩ ብቅ ብሎ አያውቅም ትዳር መስርቶ ራቅ ያለ ሌላ ቀበሌ ይኖራል ቤቱ ዘመናዊና ኑሮው የተደላደለ ሆነ።ከሰፍር ሰዎች ሰጠኝን እንደልጅ ካሳደጉት ወስጥ አንዱ አባ ንጉሴ ናቸው።አባ ንጉሴ በሰፈር የተከበሩ እና በተለያዩ የጓሮ አትክልቶች እና ዛፎች የተዋቡ ሰፊ ግቢ ያላቸው ሰው ናቸው።የከተማው መዘጋጃ ቤት የአባ ንጉሴን ቤት ሸንሽኖ መኖሪያ ቤት ለሌላቸው ሰዎች መስጠት ፈለገና ቤታቸውን ብቻ አስቀርቶ ቀሪ መሬታቸውን ሸንሽኖ ሰጠባቸው።አባ ንጉሴም ለዚሁ አቤቱታ ወደ ከተማው መዘጋጃ ቤት ሹም ሲሄዱ በኃላፊነት ቦታ ሰጠኝን አገኙት።እሱን በማግኘታቸው ደስ አላቸው ያሳደጉት ልጃቸው ለወግ ለማዕረግ በቅቶ እሱ ደግሞ በተራው የአባቱን ውለታ ሲከፍል ታያቸው ማነው የአባቴን መሬት የነካ! አባ ንጉሴ እኳ አባቴ ናቸው ባልጠፋ መሬት እንዴት ወደ እዛ ትሄዳላችሁ አሁኑኑ በቀጥታ ይሄ ነገር እንዲቆም ብሎ ሰጠኝ በብስጭት እና በቁጭት በጎናቸው ሲቆምላቸው ታያቸው ጸሃፊዋ ይግቡ አለቻቸው አባ ንጉሴን ወደ ሰጠኝ ቢሮ።

አባ ንጉሴ ወደ ቢሮ ሲገቡ ሰጠኝ ቁጭ እንዳለ ይቀመጡ አላቸው ከመቀመጫው ተነስቶ ሲጠመጠምባቸው ነበር የታያቸው ግን እንደማያውቃቸው ሆነ አባ ንጉሴ ቀይ ፊታቸው ደም ለበሰ "ለምን አሉ"?

"ምን ነው ሰጠኝ እኔን አላወከኝም አሉት"?

"እረ አውቆዎታለሁ" አለ በተረጋጋ እና በጎረነነ ድምፅ ቀጠል አድርጎም

" ለምን ጉዳይ ነበር የመጡት"?አላቸው

"እህ ያው እንግዲህ አንተም ታውቀው የለህ የእኔ መሬት የጓሮ አትክልት የማስተካከልበት አረንጓዴ ዛፎችን እያየሁ የምደሰትበት የውፎች ማደሪያ በአጠቃላይ የአካባቢው ውበት ነው ላላጡት ቦታ መጥተው ሸንሹብኝ ለእዛውም አንተ ልጄ እያለ አሉት ከጎናቸው እንዲቆምላቸው በአፅኖት እያሳሰቡ፡፡

"አዩ አባት አላቸው"

"ምን አልከ"? አሉት ስሜታቸውን መቆጣጠር እያቃታቸው ከንፈራቸው ተንቀጠቀጠ "እኔን ሳይሆን ወንበሩ ነው ማየት ያለብዎ ማለቴ እኔ ከዚህ የተቀመጥኩት ህዝብና መንግስት በእኩል ዓይን ማስተዳደር እንዳለብኝ አምኖብኝ ነው እዚህ ቦታ ላይ የግለሰቦችን ፍላጎት በዘመድ እና በዕውቅያ እናስተናግድም ይቅርታ ? ብዙ ሰዎች በቤት ችግር እጦት እየተሰቃዩ ነው እርሶም ደግሞ ከመኖሪያ አልፎ የሚቀብጡበት ትርፍ አገር መሬት አልዎት ለማንኛውም ይሄን መንግስት አምኖበት በመግስት ፕላን እና ትዕዛዝ የሚሰራ እንጂ እኔ በግሌ ያደረኩት ነገር አይደለም" አላቸው አባ ንጉሴ ከመቀመጫቸው ተነሱ "አንተን አሳድጌ እንዲህ ትለኛለህ! አባትህን ሰጠኝ ? እኔን እንዲህ ታደርገኛለ አንተ ነህ ሂዱና ንጠቁት ብለህ የለከብኝ እኛ ለአንተ ከፉ ነን አብልተን አጠጥተን አልብሰን ባሳደግን ለወግ ለማዕረግ ባበቃንህ" አባ ንጉሴ አዘኑ ሰጠኝ አሁንም ረጋ ብሎ "አባት ለቁጣዎ ምክንያታዊ ይሁኑ ሰው ባለበት አይኖርም እዚህ አገር ብዙ ጭቁን ህዝቦች አሉ እርሶዎ ደግሞ ቡርዣ ነዎት ጭቁኑ ለጎን ማረፊያ ቤት አጥተው እርሶዎ ያንን የሚያክል መሬት ታቅፈው መኖር አይችሉም የተማርነውም ይህንን የመሰለ ለውጥ ለማምጣት ነው እንደ ሰው ያልተቆጠሩትን ወዝ አደሮችን እንደ እናንተ ሰው ተብለው እንዲጠሩ ነው ለማንኛውም ጨርሺያለሁ"አላቸው። አባ ንጉሴ ጮሁ እውነት በእጁ እንዳልበላህ እውነት የአንተን ነገር እያሉ ወጥተው ሄዱ

በሚቀጥለው ቀን የከተማው ከንቲባ ሰጠኝ ጎበዜ የመስሪያ ቤቱን ሰራተኞች ስብሰባ ጠራ። " ይሄውላችሁ ዛሬ እናንተን የሰበሰብኩት ዋናው ምክንያቴ በስራችሁ ቁርጠና እንድትሆኑ ለማሳሰብ ነው ምን ጊዜም ቢሆን ለዘብተኛ መሆን የለባችሁም አንዳንድ ከበርቴዎች የተለያየ ነገር ሊናገሯቹ ይችላሉ ግን እኛ የቆምነው ለድሆች መሆኑን መረሳት የለምበትም ድሆችም መኖር አለባቸው እነዚህ ጭቁኖች ደግሞ እንዲኖሩ ማድረግ ያለብን እኛ ነን ከአቅም በላይ የሆነ ቡርዣ ካለ እና ከረበሸ በአስቸኳይ ለእኔ ሪፖርት አድርጉ ለፖሊስ ደውለን ማሳሰር እንችላለን ይህንን የቆየና የሻገተ አመለካከት በአንድ ጊዜ በማስተማር መቀየር አይቻለም ስለሆነም አልፎ አልፎ ኃይልን መጠቀም ግድ ይላል ጨርሺያለሁ ጥያቄ ያላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ"አለ ምንም ጥያቄም አስተያየትም የለም ስብሰባው አለቀ ሁሉም ካአዳራሹ ሲወጡ አንዱ መሃንዲስ ወደኋላ ቀረና ሰጠኝን በጆሮው እንሾካሾከው ማታ ላይ ከተለመደው ቦታ ብሎት ወጣ።





ሰጠኝ ከተማዋ በእጁ ስር ወደቀች ቦታ ፈላጊው ኢንቨስተሩ በተለያየ ጉዳይ ወደ ከንቲባው ቢሮ የሚሄዱ ሁሉ ጉዳያቸው የሚታየው በሚሸጉጡት የጉቦ ጉርሻ ሆነ ሰጠኝ ደለበ ሰውነቱ አበጠ!ሰጠኝ በየቀኑ ማታ ማታ ውስኪ ሲጠጣ ከፈለገው ሴት ጋር ሲማግጥ የፈለገውን ሲናገር ያመሻል ማንም ቀና ብሎ አያየሁም ማንም ደፍሮ መጥፎ ንግግር አያናገረውም።

ወደ ዴንሳ ቡና ቤት ሲሄድ በቀጥታ ዴንሳ ወደ ውስጥ ብቻውን ይዛው ትገባለች ለዴንሳ መሃል ከተማው ላይ ለዘመናዊ ሆቴል መስሪያ ቦታ ሰጥቷታል በዴንሳ የሚመጣ ነገር በሙሉ ይቀበላል ዴንሳ ከራሷ አልፎ ለብዙ ሰዎች ውለታ ውላለች።ሰጠኝ ትዳሩን መናቅ ሚስቱን ማንቋሸሸ ከጀመረ ሰነባበተ።የሰጠኝ ግፍ በከተማው ህዝቦች ላይ የሚያደርገው ነገር በሙሉ የጉበው ግርግር እና የንጹሃን ዜጎች ፍትህ ማጣት ወሬው ወደ ላይኛው የስልጣን እርከን ወዳሉት ሰዎች ጆሮ ደረሰ ከፍተኛ ባለስልጣናትም ለሁኔታው ትኩረት በመስጠት የከተማውን ከንቲባ ፅህፈት ቤት ሰራተኞች የግምገማ ስብሰባ አዘጋጅቶ እነ ሰጠኝን አስገመገመ ሰጠኝ እያንዳንዱ የሰራት ነገር ለባለስልጣናቱ አንድ ባአንድ ተነገራቸው ባለስልጣናቱም ሰጠኝን የተባልከውን ነገር ትቀበላለከ ወይስ አትቀበለም አሉት ሰጠኝም ከተባሉት ውስጥ ባለማወቅ የፈጸምኳቸውን ግማሹን እቀበላለሁ ሌላው ነገር ግን የተጋነነ ስለሆነ አልቀበለውም አለ።በመጨረሻም ባለስልጣናቱ ሁኔታውን ካዩ እና ከገመገሙ በኋላ ሰጠኝ የፈጸመው ወንጀል ለይቅርታ ሊያበቃው ስለማይችል ከስራ አሰናበቱት።

ሰጠኝ ያንን የመሰለ ስራውን እና ክብሩን አጣ ጠወለገ ተሰፋ ቆረጠ  ሚስቱም ያንተ ግፍ ገና ወደ ልጆች ይመጣል ትዳርህን እና ህዝብህን የረሳህ እና ያዋረድከ ሰው ነክ ከእንግዲ  እኔም ከአንተ ጋር አልኖርም ብላ የፍቺ ከስ መሰረተች ፍርድ ቤቱም የሰጠኝን ጥጋብ ያውቅ ነበር እና ቤቱን እና ያለውን ነገር ለሚስቱ እንዲሆን የውሳኔ ብይን አስተላለፈ የሚስቱ አባት ልጃቸውን ተቆጡ ተይ ልጄ ያለፈው አልፎል የልጆችሽ አባት ነው ሁሉን ነገር ይቅር በይው ከእንግዲህ ልቦና ይገዛ ይሆናል ብለው ለማስታረቅ ሞከሩ ልጃቸው ግን በፍፁም አላች።

ሰጠኝ ታመመ ሆስፒታል ገብቶ የሚታከምበት ገንዘብ እንኳን የለውም ድሮ አባቱ ይጠጣበት ከነበረው ፀበል ሄደ ፀበል መጠጣት ጀመረ ከፀበል በኋላ ተውልዶ ወዳ አደገበት ሰፈር ሄደ ያሳደጉት የሰፈሩ ሰዎች ባዩት ጊዜ ልባቸው አዘነ የእዛች የደግ ሴትዩ የአቻሽ ልጅ ሁሉም ተንከባከቡት ተረባረቡለት።

ሰጠኝ የአባ ንጉሴን ግቢ አየሁ የድሮ ውበት የለም ዛፎች የጓሮ አትክልቶች የሉም ሌሎች ሰዎች ቤት ሰርተውበታል ።ያ በልጅነቱ የሚያውቀው የአባ ንጉሴ ቤት ግርማ ሞገሱ ጠፍቷል አባ ንጉሴም የሉም መንነው ገዳም ገብተዋል።

# እህል ውሃ

አውሊያው በረኸኛ
በረኸኛው
አውሊያው በረኸኛ......በረኸኛው
እኔ አላጎራውም .......... በረኸኛው
ይሄን ጉሪ ብዬ............በረኸኛው
ቆረቆንዳው ወጥቶ.......በረኸኛው
አብቁ ካለየ.................በረኸኛው
እንግዲህ ጀመረ
ምሪድ አንጠራራ
ያንዱን ቤት አፍርሶ
ያንዱን ቤት ሊሰራ

ከሸህ አደም ቤት ዘውትር ሰኞ እና ሐሙስ ሌሊት ድቢና ጭብጨባ ከእልልትና ከጉሪ ጋር ሲቀልጥ ያድራል።ሸህ አደም ደሴ ውስጥ እሉ እና እንቱ የተባሉ ጠንቋይ ሸህ ናቸው። በእድሚያቸው ብዙውም ያልገፉት ወጣቱ ሸህ አደም ቀይ መልከ መልካም አልፎ አልፎ ኩል የሚኳሉ እና እጃቸውን እንሶስላ የሚሞቁ ባለ ብዙ ዛር ገበር ናቸው።ቤታቸው ወደ ኩታ በር መውጫ የደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅን አልፍ ብሎ በስተግራ በኩል ጦሳ ተራራ ስር ነው።የሃድራቸው ቀን የለሊቱ ዲማቅ ከጦሳ ተራራ ገደል ማሚቱ ጋር ሲያስተጋባ ያድራል ቤታቸው ሰፊ ጊቢ ሆኖ ከበር ላይ ወይራ ውስጥ ደግሞ የተለያየ ዓይነት ጭስ ስለሚጨስ ከርቀት የሸህ አደም ቤት እዚህ ነው ብሎ ይጣራል።ሸህ አደም ሰፊ መስጊግ አላቸው የመስጊዲ ግማሹ አካል በትልቅ ቀይ መጋረጃ የተጋረደ ሲሆን ከመጋረጃያው ወዲህ የወንዶች ከመጋረጃው ወዲያ የሴቶች ክፍል ነው።ሸህ አደም ትልቅ ጥምጣማቸውን ጠምጥመው በሁለት ጉንጫቸው የጫት ተርዚናቸውን ወጥረው ያጉረመርማሉ

ተው እነት ውሽታም አሳማ
ተው ሸሆቱን አትማ
ሃዩ መሌ.............ሃዩ መሌ
እያንጎራጎረ ወጣ ጎራውን
እልታይው ብሎ ሃይባ እና ቁባው........
ሃዩ መሌ.............ሃዩ መሌ...............

አሜን ብሎ ይቀበላል ሃድራው ላይ ሶፋ ሰርቶ የተሰተረው ባለ ሃጃ ደንበኞቻቸው።ሸህ አደም ቤት የሁሉም ኃይማኖት ተከታዩች ይሄዳሉ ከእኝህ ሸህ ቤት ልጅ መውለድ ያልቻለ፣ ንግድ የጠመመበት፣ትዳር አልወጣ ያለው፣በሽታ የሚያሰቃየሁ የተለያየ ፍላጎት ያለው ሰው





በአንድ ግቢ በሸህ አደም ቤት ተሰብስቦ በሸህው ዱዓና ቱፍታ ከተቀየዱበት ችግር መፈታት ይፈልጋሉ ደረቅ ሌሊት ላይ ድቢ እየተመታ የአውሊያ ዘፈን ሲዘፈን ዛር ውቃቢ ያለባቸው በሙሉ ያጎራሉ ገበሩም አንድ ባአንድ ዛሩን ይጠይቁታል ያናግሩታል "ወሪም ሰላም ማለኩም አንተ ማነህ"?
"እኔ ሰያሬ ጨንገሩ ነኝ"
"ዓለሜ እኛንም ፈረስህንም እፉ በል"እያሉ ዛሩን ከፈረሱ ጋር ሲያስታርቁ ሲያስደስቱ ያድርሉ።የሸህው መስጊድ በጀባታ ዕቃ የተሞላ ነው የተለያዩ ጀቦታ ይመጥላቸዋል
ሸሆቹ ..............................ኮርማ ጀባ
ሸሆቹ..............................ወርቅ ጀባ
ሸህ አደም ይመርቃሉ
.......................... "ሃጃችሁ ይውጣ............................አሜን
.......................... "አሲዳችሁን ይጣለው.....................አሜን
ቁሜ አድምጩ .......ይኽ ሩጨን ይያዝልን..................አሜን
ከዛህም ወደ ጊቢው...................እንደገና ጭብጨባ ይደምቃል እንደገና የዛር ዘፈን ይዘፈናል።

ከሸህ አደም መጥቶ ምን ጠፍቶ የሸህው ከዳሚዎች ስለ ሸሆቻቸው ተሰጦ ይናገራሉ "አንድ መኪና ተገልብጦ ሸህ አደም መጀን ያለችሁ ስትተርፍ ሌሎቹ አለቁ............አንዱ ጎብጦ መቃናት አቅቶት ከተለያየ ሃኪም ቢሄድ ያልተሳካለትን ሸህ አደም እንትፍትፍ ሲሉበት በአንድ ጊዜ ቀጥ ብሎ ሄደ.............አንድ ነጋዴ ከስሮ ከአሳቸው ተመርቆ ከሄደ በኋላ ሚሊየነር ሆነ......................!"አሜን ይላል አድማጭ ሃድራው ላይ የተሰበሰበ ባለሃጃ ...... "ለኛም ይድረሱልን...............ሸህ አደም መጀን በእርሶዎ ይሁንበት.."

አንዲት ቀይ አጭር ቀንጆ መልከኛ ሴት ባሏ እና ሁለት ወጣት ሴት ልጆቿ ደግፈው ወደ ሸህ አደም ግቢ ይዘዋት ገቡ።ትጮሃለች ትለፈልፋለች ሸህ አደም ልቀቋት አሉ ተነሱና በጉማሬ አለንጋ ነካ ነካ አድርገው ፊቷን በጫት ቱፍታ ሲገርፏት ይበልጥ ጮሀች ሸህ አደምም ወደ መስጊዳቸው ይዘዋት ገቡ ዲቢያቸውን አቅርበው በረኸኛው አውልያ የዛር ዘፈን አቀነቀኑለት። ዓለምነሽ ጉራዋን ሰጠሰጠችው
ወረም "ሰላማ አሌኩም" አሉት ዛሩን
"ማዕለኩ ሰላም" አለ እየተኮላተፈ
"ማነህ አንተህ?ለምንድ ነው እንዲህ የምታስቸግራት?ቤተሰቦቿንም ለምን ትረብሻለክ? አሳዳሪዋንም ስራ አስቁመህ እንከራተትከው ምንድ ነው የበደለክ" አሉት
ዛሩም "እኔ ሃብቴ ሸለላው ነኝ ........በረኸኛው አውሊያ ነኝ ቤት የባሩድ ሽታ ስፈልግ ባሩድ አያጨሱልኝም አሳዳሪዋም ይንቀኛል ፈረሴን አትዙሪብኝ ቁጭ በይ ሰላት አትሰማኝም"አለ
"በል አለሜ ሰው አጥፊ አውሊያ ማሃሪ ነው እፉ በላቸው አሁን ከስፍራህ መጥተሃል ሁሉን

በመደድ በመደዱ እናደርገዋለን ምልክት አሳይ አፉ በል አለሜ" እያሉ ለመኑት አውሊያውም የገባሩን የሸህ አደምን ልመና ተቀብሎ አፉ አለ።

ከዛን ቀን ጀምሮ አለምነሽ ባለቤቷ አስማረ እና ሁለቱ ልጆቿዋ የሸህ አደም ልጆች ሆኑ ዘውትር ሰኞ እና ሐሙስ ከሃድራው ከጀማአው ከጨብጭበው ከእልልታው ከቂማሃው ከዱአው አይቀሩም።አስማረ ባለአንድ ካቻማሌ መኪና እና ባለ አንድ ትልቅ ግሮሰሪ ባለቤት ነው ሁሌም ጀባታ እየያዘ ይሄዳል ሸህ አደም ትልቅ ባለውለታው ናቸው የልጆቹን እናት ከዛ ከፉ ደዌ ፈውሰውለታል። እንደ አባት ያያቸዋል ያከብራቸዋል ይወዳቸዋል።

አንድ ቀን ቂማሃ ላይ ሸህ አደም አስማረን ጠሩትና "ከእንግዲህ የመኪና ስራ አይሆንህምና መኪናህን ሸጠው ሳትሰራ የምትከብርበትን የታየኝን እነግርሃለሁ ከደሴ ወድ ኮምፖልቻ በሚወስደው የሃረሳ መንገድ መጨረሻ መውረጃው በስተቀኝ አንድ ትልቅ ዛፍ አለ እዛ ዛፍ ስር ጣሊያን የቀበረው ጠገራ ብር አለ ያንን ጠገራ ብር ለማውጣት ጥቁር በግ ጠርሙስ አረቄ እና በጣም ጥቁር የሆን ትንሽ ልጅ አርደ ቅበር ከዛ በኋላ አዱኛ የተባለ በአንተ እጅ ይሆናል"አሉት። ከፈጣሪ ቀጥሎ ሁሉ ነገር የሚታያቸው ሸህ አደም ናቸው በአስማረ አስተሳሰብ እኚህ ሸህ ትላንት ባለቤቱን ፈወሱለት አሁን ደግሞ ትልቅ ሃብታም ሊያደርጉት ነው "እሺ አባቴ" ብሎ ጉልበት ሳመ..............................።

አስማረም የተባለውን ቦታ አጠና በጣም ሚስጥር በሆነ ሁኔታ ሁለት ሰዎችን ቀጠረ ሁለቱ ሰዎች ከየት እንዳመጡት ባይታወቅም አንድ ጥቁር የሆነ ምስኪን የደሃ ልጅ አታለው ይዘው መጡ በለሊት ወደ ቦታው ሄዱ..... በጉን እና ልጁን ለመሰዋት አቀረቧቸው ልጁን እዛው ከበጉ ጋር ቀበሩት።

ተቆፈረ ተቆፈር ጣሊያን የቀበረው ጥሬ ብር ግን አልተገኘም ተቀጣሪ ሁለቱ ሰዎች የለፋንበትም ይሁን ይህንን ሁሉ ኃጢያት የሰራንበትን ገንዘባችንን ክፈለን አሉት አስማረ "እንዴት ልከፍላችሁ እችላለሁ ጥሬ ብሩ ቢገኝ ነበር አሁን ከየት አምጥቼ እከፍላችዋለሁ" አላቸሁ ከርከሩ ወድ ለየለት ፀብ አምርቶ ሰዎቹ ሁኔታውን ለፖሊስ አስረዱ አስማረ በቁጥጥር ስር ዋለ በቂ ማስረጃ ስለተገኘበት ወይን ወረደ።

አስማረ ወህኒ ከወረደ ወዲህ የዓለምነሽን ቤት ቀዝቅዟል በቂ ገንዘብ የለም ዓለምነሽና ልጆቿ እንኳን የሚዝናኑበት የሚበሉት እያጡ መጡ በዛ ላይ ዓለምነሽ ከሸህ አደም ፀንሳ ነፍሰ ጡር ነች።ዓለምነሽ ሴት ልጇን ተገላገለች ሸህ አደምን እንዲረዷት ጠየቀች ሸህ አደም ግን ወልደው ካዱ ሁለትኛ ቤቴ አካባቢ እንዳትደርሺ ብለው ለአንዴና ለመጨሪሻ አባረሯት።

የአቶ አስማር ቤትና ቤተሰብ ተበተኑ ሴት ልጆቻቸው አዲስ አበባ ገብተው ሴተኛ አዳሪነት ጀመሩ።





ዲያስፖራው ዳኒ ከጓደኛው ዮናታ ጋር አዲስ አበባን እያዳረሷት ነው ቀን ላይ ምሳ 22 ማዞሪያ አካባቢ ዮናስ ክትፎ ቤት ምሳ በልተው እዛው አካባቢ ቅመው ማታ ላይ ቺቺኒያ ወደ ተባለ ብዙ ደስተኛ ወጣት ሴተኛ አዳሪዎች ወደአሉበት ይሄዳሉ።ዲያስፖራው ዳኒ ወደ አዲስ አበባ የመጣበት ዋንኛው ምክንያት ለሚስትነት ያጫትን አሜሪካን አገር ሆኖ ለአራት ዓመታት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሳይጠረጥራት በእውነተኛ ልቡ አፍቅሮ የወደፊት ሚስቱ ያላትን ሜሮንን ለማግባት ነበር። ሜሮን በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የአራተኛ ዓመት የህግ ተማሪ ነች።አራቱን ዓመት ተቸግራ ኢታውቅም ዳኒ በጣም ጥሩ አፍቃሪ ነው አንድም ቀን ሳያሳልፍ ለአራት አመት ሙሉ በየወሩ ዶላር ይልክላት ነበር ሜሮን ከራሷ አልፎ ለጓደኞቿ ትተርፍ ነበር።ቀኑ ደረሰና ዳኒ እና ሜሮን ተገናኙ ዳኒም ከሜሮን ጋር ጋብቻውን ፈፅመ ወደ አሜሪካን ሃገር ፕሮሰስ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ ነገራት ሜሮን አንስታ ስልክ ደወለች ከደቂቃዎች በኃላ አንድ ጎረምሳ ልጅ መጣ ዳኒን ሰላም ብሎ የሜሮን ጉንጭ ስሞ ተቀመጠ።ሜሮን ዳኒን አተኩራ እየችሁ "እየሀ ዳኒ!"አለችው "አንተ በጣም ጥሩ ሰው ነህ እኔም ብዙ ጊዜ ከውስጤ ጋር ተሟግቺያለሁ ይቅርታ ልወድክ አልቻልኩም እኔ ጓደኛ አለኝ ጓደኛዬም ይሄ ነው"አለችሁ አገጯን ወደ ልጁ እየጠቆመች ዳኒ የሰማውን ማመን አልቻለም ተነስቶ ለዮናታ ደውለለት ዮናታ "ተረጋጋ ተረጋጋ የዘሙት ሴቶች እንዲህ ናቸው ሴት ሞልቷል ሁሉም ነገር ለበጎ ነው" እያለ ያጽናናዋል ዮናታ ደረሰለት የዳኒን እጅ ይዞ አፅናናው።ዮናታን ድኒን ወደ አንድ ሞሮኮ ባዝ ወሰደው ሞሮኮ ባዝ ውስጥ ደንበኞችን በራቁት የሚያጥቡ ቆነጃጅት ሴቶች አሉ ዮናታን አንዷን ቆንጆ ጠርቶ በጆሮዋ አንሾካሾካት ልጅቱም ፈገግ ብላ ዳኒ ይዛው ወዳንድ መታጠቢያ ክፍል ይዛው ገባች ጨርሰው ሲወጡ ዳኒ ትንሽ ተርጋግቷል ቀኑ መሸ ቺቺኒያ ግን እየነጋ ነው ዮናታን ዳኒን ወድ ቺቺኒያ ወሰደው ከመጀመሪያው ባር ውስጥ ገቡ ጋብዙን ብለው አራት ሴቶች ከበቧቸው አንድ አንድ ቢራ ጋበዟቸው ወደ ሚቀጥለው ቤት ሄዱ እያሉ እያሉ እኩለ ለሊት ላይ አስፓልቱን ተሻግረው ወንዲ ማከ አንቺ ልጅ ምን ይጥራሽ"የሚለው ዘፈን ወደ ተከፈተበት ቤት ገቡ አንዲት ቀይ ቀጠን ያለች ረጅም መልከኛ ልጅ "ምን ልታዘዝ አለቻቸው? ዳኒ አተኩሮ አያት "ነይ እስቲ ማነው ስምሽ?አላት

"የሺ"አለችው

"የሺ ቁጭ ሜሮንን ነው እኮ የምትመስይው"አላት

"ሜሮን ማን ናች? አላውቃትም" አለችው በሰከረ እና በተጎላደፈ ምላሱ "ሜሮን እኔን የሸወደችን በሙቶት ያፈዘዘችኝ" እያለ ሲለፈልፍ የሆነ ነገር እንድሆነ የሺ ገመተች "በቃ እሷን እርሳት እኔ እለሁል ከአሁኑ ጀምሮ ያንተ ነኝ ብላ በእቅፍ ውስጥ ገባች። እንደ ሜሮን ከፉ ከሃዲ ነሽ!!!!" አላት

"አይደለሁም"አለችሁ እየጠጡ ነው ሙዚቃውም ድምፅ ጨምሮ ቤቱ ሞቋል እረ እንዴት ነሽ አንቺየ እያለ ሲዘፍን ዳኒ እሪ እንዴት ነሽ የሽዬ ይላል እኩል ከሙዚቃው ጋር "በእናትከ ተወኝ ልቤ ሥሥ ነው ፍቅር እያዝብሃለሁ" አለችው
"እና ምን ችግር አለ እንኳን ላፈቀርሽኝ ለጠላቴ የሆንኩ ሰው ነኝ ካፈቀርሽኝ አፈቅርሻለሁ"አላት ዳኒ የሺን ይዞ ለአዳር ወጣ አብረው አደሩ ጠዋት ላይ በተረጋጋ መንፈስ ማውራት ጀመሩ የሺ የዳኒ ገራገርነት ገብቷታል ከሁኔታው ጥሩ ሰው እንደሆነ እና የተጎዳ መሆኑን ተገንዝባላች።
"ምንድነው የሆንከው?የት ነው የምትኖረው?ማታ እኮ ደህና አልነበርከም!ሜሮን ሜሮን ስትል ነው ያደርከው"አለችሁ።ዳኒ የሆነሁን ሁሉ ለየሺ አጫወታት ዳኒም በተራው "አንቺ ለምንድ ነው ወደ እዚህ ስራ የገባሽው እኔ እዚህ ስራ ላይ የማያቸው ሴቶች በሙሉ ያሳዝኑኛል ምክንያቱም ዓለም ከፍታባቸውና ፊቷን አዙራባቸው እንደሆነ ይገባኛል!!"
"አዛኝ መሆንህ ታስታውቃለህ ማታ ላይ ሙተት ነው በሙተት ነው እንዲህ ያደረገችኝ ሜሮን ስትል የእኔን ቁስል ነካህው እየህ ዳኒ የብዙ ሰው ሕይወት የተበላሸው አገራችን ውስጥ ሙተተኛ፣ጠንቋይ፣ደብተራ የሚባል ነገር ስላለ ነው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ብዙ ሰው ከነቤተሰቡ የዚህ ጎጂ ባህል ሰላባ ነው።የእኔ አባት ጠንካራ ሰራተኛ እና ቤቱን በስነ-ስረዓት የሚያስተዳድር ነበር አይጠጣም፣ አያጨስም፣ አይሸረሙጥም ሸከፍ አድርጎ ነበር ያሳደገን በኋላ ላይ ግን እናቴ ዛር የሚባል በሽታ አሟት አባቴ ጠንቋይ ቤት ወሰዳት ጠንቋዩ ግን መጨረሻ ላይ በታተነን እናቴን ለመርዳት ስል እኔም ወደዚህ ስራ" ገባው አለችሁ።ዳኒ አዘን ልቡ ተነካ የሺ የሚወዳትን ሜሮንን ነው የምትመስለው ቀን ላይ ሜሮን ከዳው ማታ ላይ ሜሮንን አገኛት አሁን ላይ የሜሮንን ህይወት ተዘባርቆ እቅፍ ውስጥ አለች አይኖቹ እምባ አቀረሩ "እሺ ቢቃ አሁን እንነሳ እና ማታ ላይ እንደገና እንገናኛለን ከጓደኛዬ ጋር እመጣለሁ" ተባብለው ተለያዩ።ቀኑን ሙሉ ዳኒ ለዮናታን ስለየሺ ሲያወራው ዋለ እንዳዘነላት እንደወደዳት አስረዳው እናም እሷን ማግባት እንድሚቀል ገለጸለት ዮናታን ግን አልተቀበለውም "እንዴት ሴተኛ አዳሪ ታገባለህ አራት ዓመት ሙሉ የረዳሃትና ያስተማርካት ያልሆነችህ እንዴት ሴተኛ አዳሪዋ ትሆናሃለች ብለ ታስባለህ" አለው "ቢቃ ትጉዳኝ የሺ ከዚህ ህይወት ትውጣ እንጅ ትጉዳኝ ቢያንስ ቢያንስ ህይወቷን ማስተካከል ከቻልኩ ለእኔ ትልቅ ነገር ነው" አለው "ካልከ ምርጫው ያንተ ነው"አለው ዮናታ።
"በእናትህ ፒያሳ እንሂድ" አለውና የወርቅ ሃብል እና ቀለበት ገዝቶ ማታ ላይ የሺ ካለችበት ባር ገቡ ሲጠጡ አመሹ የሺ አብራቸው ትጠጣለች።
"የሺ" አላት ዳኒ
"ጓደኞቼ የምትያቸውን በሙሉ ጥሪያቸውና የሚገልጉትን መጠጥ ስጪልኝ?"አላት እሷም ሁሉን ጋበዘች ዳኒ ወደ ባሩ ባለቤት ጠጋ ብሎ "የስርግ ዘፈን ከፈቺልኝ"አላት ባለቤቷም





ፍላጎቱን እሟላችለት ዳኒ የየሺን እጅ ይዞ ተንበረከከ ውስጥ ያሉት በሙሉ ህልም ወይም ፊልም መሰላቸው ግማሾች አይ ሰካራም እያሉ ይሰቃሉ።
"የሺ!!!!" አላት ዳኒ "ከዛሬ ጀምሮ እኔና አንቺ ባል እና ሚስት ነን ብሎ የያዘውን ቀለበት ጣቷ ውስጥ አጠለቀው።

# ካሜራው

ሳንሆዜ ካሊፎርኒያ ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ የአየር ንብረት እንዳላት ይነገርላታል።ብዙ ሃብታሞች የሚኖሩባት ሳኖሆዜ ከሌሎች የአሜሪካ ከተሞች ኑሮ ይወደድበታል ሳንሆዜን ከሳንፍራንሲስኮ ጋር አዋህደው(Bay area) ወይም የባህር ወሽመጥ በሚል የጥቅል ስያሜ ሰጥተዋቸዋል።ሳንሆዜን የለመድ ሰው ሌላ አገር ለመኖር በእጅጉ ይቸገራል የከተማው መንገዶች እጅግ ያምራሉ እንደማንኛውም ቦታ ሳንሆዜ ውስጥ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ይኖራሉ የኢትዮጵያን ምግብ ቤቶች እና የሃበሻ መደብሮች አሉ ትልቁ የሃበሻ ምግብ ቤት ባለቤት ጌዲዮን ከባለቤቱ ትዝታ ጋር የመጀመሪያውን ሬስቶራንት የከፈቱ ናቸው።ጌዲዮን እና ትዝታ እንደ ባል እና ሚስት ብቻ ሳይሆን እንደ እህት እና ወንድም ተሳስበው ተዛዝነው ለዚህ ውጤት እንደደረሱ ብዙዎቹ ይመሰከሩላቸዋል ሁለት ወንዶች እና አንድ ሴት ልጆችም አፍርተዋል።

ጌዲዮን ተኝቶ አርፍዶ አምሽቶ ይገባል ትዝታ ደግሞ ማለዳ ተነስታ በጊዜ ወደ ቤት ትገባለች።1969 እ.ኢ.አ ጌዲዮን በመሃል አዲስ አበባ አሉ ከሚባሉ የኢ.ህ.አ.ፓ ትግል አመራር ውስጥ አንዱ ነበር አገራችንን የእነ እስታሊን እና ሌኒን የሶሻሊዝም ርዩተ ዓለም ባናወጣት ጊዜ ህዝባዊ መንግስት ይመሰረት ህዝባዊ ኢህአፓ ይለምልም እያሉ ከወታደራዊ መንግስት ጋር የሞት ሽረት ትግል አድርገዋል።የኢህአፓ የከተማ ውስጥ ትግል እየጠወለገ ሲመጣ ጌዲዮን ከመሃል አዲስ አበባ ወጥቶ ወደ ደብረ ማርቆስ ሸሽቶ ሄደ ደብረ ማርቆስ እንደ ደረሰ ከተማው ውስጥ ከተደራጁት የኢህአፓ የትግል አጋሮቹ ጋር ተቀላቀለ ከታጋዮቹም ውስጥ ትዝታ አንዷ ነበርች ደብረማርቆስ ለኢህአፓዎች አመቺ አልነበረምና በአገው ምድር አቋርጠው ወደ ሱዳን ጠረፍ ለመሸሽ ወስነው ጉዟቸውን በለሊት ጀመሩ። ጉዞው ፈታኝ ነበር ርሃቡ፣ውሃ ማጣቱት፣ተንኳሽ አውሬው ብቻ በሞት እና በህይወት መካከል ሆነው ሱዳን ጠረፍ ደረሱ የገጠር ቀመስ ልጆች በረሃውን በከፊል መቋቋም ሲችሉ ጌዲዮን ግን የወባ ትንኝ ነድፋው በወባ በሽታ ወደቀ ዛሬ ይሞታል ነገ ይሞታል ዓይን ዓይኑን ይታይ በነበረበት ጊዜ ከጎኑ ሳትለየው ያስታመመችሁ ትዝታ ነበረች።ቀኗ ያልደረሰ ነፍስ አትወጣም እና ጌዲዬን ከሞት ተረፈ ከህመሙ በኋላ ግን በረሃ ላይ መኖር አልፈለገም ብዙ ነገር ከትዝታ ጋር ያወራሉ ይወያያሉ ጌዲዮን ትዝታን ወደ-ታል ትዝታም ጌዲዮንን ወዳዋለች ሁለቱ ተነጋግረው ጠፉ እንደምንም ካርቱም ሱዳን ገብተው የግል ህይወታቸውን መኖር ጀመሩ የመጀመሪያ ልጃቸውንም ወለዱ ካዛ አሜሪካ ኤምባሲ የኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በሱዳን ወደ አሜሪካን መውሰድ ሲጀመር ጌዲዮን እና ትዝታ ተመዝግበው ዕድል ቀንቷቸው ሳንሆዜ ካሊፎርኒያ ገቡ።

ሳንሆዜ ገብተው ስራ ጀመሩ የሃበሻው ቁጥርም እየጨመረ መጣ እነ ጌዲዮን ብዙ የሃበሻ እንግዳ እየተቀበሉ ማላመድ ጀመሩ ጓደኞችም አፈሩ ያንን ሁሉ አልፈው





የመጀመሪያውን የሃበሻ ምግቤት በሳንሆዜ ከፈቱ።ፈረንጆቹ የኢትዮጵዊያንን ምግብ ወደዱት የነጌዲዮን ምግብ ቤት በየቀኑ መድመቅ ጀመረ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ልጆችም ወለዱ በስራቸው ስለተሳካላቸው ዘመናዊ ቤት ገዙ ሁሌም ደስተኞች ናቸው አመት በዓል ሲሆን ብዙዎቹ ኢትዮጵያዊያን ከእነ ጌዲዮን መኖሪያ ቤት ይሰበሰባሉ አመት ባዓሉን አብረው ያሳልፋሉ።ምግብ ቤቱን ጠዋት ትዝታ ትከፍታለች ማታ ጌዲዮን ይዘጋል ትዝታ ቀድማ ወደ ቤት በመሄድ ቤት ውስጥ የሚያስፈልገውን ነገር ታዘጋጃለች ጌዲዮን አጸዳድቶ ዘግቶ ሲመሽ ወደ ቤቱ ይገባል።የጌዲዮን ጓደኛ መሃሪ ምሽት ላይ በተደጋጋሚ እንግዳ የሆነ መኪና ከነ ጌዲዮን ግቢ ቆሞ አይቷል ለጌዲዮን አልነገረውም ለብዙ ጊዜ ተከታተለ ትዝታ ወደ ቤት በምትገባበት ሰዓት ላይ መኪናው አለ ጌዲዮን ወደ ቤቱ መሄጃ ሰአት ላይ መኪናው አይኖርም መሃሪ ጊዜውን ወስዶ በጥንቃቄ አንድ ጎረምሳ ጃማይካዊ ነው መሃሪ ይህንን ነገር ለጌዲዮን ለመናገር ወሰነ መሃሪም ጌዲዮንን ማታ ላይ ወደቤት ከመሄድ በፊት እፈልግሃለሁ ብሎ ተገናኙ ያየሁን ሁላ በእርጋታ አስረዳው ጌዲዮን በመሃሪ ላይ እንባረቀበት "ስማ ቀንተ ነው አይደል እኔ እና ትዝታ እንዴት እንዴት እንደተገናኘን ታውቃለህ እንኳን አንተ ሰይጣን እያለያየንም ምቀኛ ሁለተኛ ቤቴ አካባቢ እንዳትደርስ" ብሎ መሃሪን አዋረደው በኋላ ላይ ግን ጌዲዮን ስለሁኔታው ብቻውን ማንሰላሰል ጀመረ ምናልባት አይታወቅም አለና መኖሪያ ቤቱ ትዝታ በሌለችበት በድብቅ የቪዲያዬ ካሜራ አስገጠመ።ባስገጠመ ማግስት ብቻውን ገብቶ ካሜራውን አየ የያውን ነገር ማመን አልቻለም ትዝታ ከጃማይካው ጋር የማታደርገው ነገር የላትም እርቃኗን በእርቃኑ አንስቶ ሲያቃትት ሲስማት ሲቀብጡ አየ ራሱን ሳተ ትዝታ በእኔ ላይ እንዴት እንዴት አለ የቪዲዮ ካሜራውን ይዞ ወደ መሃሪ ቤት ሄደ "መሃሪ ይቅርታ በጣም ይቅርታ ምናባቴ እንደማደርግ አላውቅም ምን አልባትም ራሴን ላጠፋ እችላለው ልጆቼን አደራ የጠረጠርከው ነገር ሆኖ አገኘሁት ቪዲዮ ካሜራ በድብቅ አስገብቼ ነበር ጉድ ነው ያየሁት መሃሪ ጉድ ነው የሆንኩት መሃሪ" "ተረጋጋ ተረጋጋ ሁሉን ነገር በብስለት መወጣት አለብህ ለውሳኔ አትቸኩል በቃ የፈሰሰ አይታፈስም አንተ እንዳወክ ማወቅ የለባትም ምንም ዓይነት የጥርጣሬ ፊት እንዳታሳያት ሰው ሲሄድ ሰው ይመጣል ይልቁንስ የለፋህበትን ወስዳ ለእሱ ደስታ ከማድረጓ በፊት ይህንን ማስረጃ ይዞ ከህግ ፊት ገትራት አለው" ጠበቃ አነጋግሮ ለትዝታ ክስ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ወረቀት ተሰጣት ትዝታም ጌዲዮን ላይ ጮህችበት "ሌባ እንደራስ መስሎ ነው ስማ ለፍቼ ያፈራሁትን ገንዘብ በሰበቡ ወደ ዘመዶችህ ለማሸሽት አይሳካልህም እመነኝ አለችሁ።"

*ቀጠሮው ደርሶ ትዝታ ዳኛ ፊት ቀረበች*

"ወ/ሮ ትዝታ ከትዳርሽ ላይ ማግጠሻል ነው ወይስ አይደለም?"ዳኛው ጠየቋት

"በፍፁም ከእውነት የራቀ ሴራ ነው ጌታዬ"አለች ዳኛውም ትዝታ ወደ ዳኛው እንድትመጣ ጠየቋትና "ይህንን የቪድዮ ምስል አሳያት ይቺ ሴት ማነች"?ሰውዬውስ

የፈቀደ ጋብቻ መስርተው ጎጆ ወጠተው የትዳር ሕይወትን ይጅምራሉ።ጎጆ ለመውጣት የሚጣጣሩት እንደ እነ ፍስሃና ደብሬ ዓይነት እስከሚጋቡ ድረስ በከንፈር ወዳጅነት ይቆያሉ።

በአንድ ምሽት እንደተለመደው ደብሬ ወደ ምንጭ ውሃ ሄደች ፍስሃ ያንን ቀን የለም ይመጣል ብላ ትንሽ ጠበቀች ፍስሃ አልመጣም ደብሬ ተስፋ ቆርጣ የቀዳችሁን ውሃ ተሸከማ ጉዞ ጀመረች። ሸምበቆ ዛፍ ውስጥ ኮሽኮሽታ ሰማች ሳታስበው በቅፅፈት ከፊቷ ላይ አንድ ሰው ትልቅ ጩቤ ይዞ ቆሟል "ምንም እንዳትጮሂ"ብሎ ማስጠንቀቂያ ሰጣት ወደ ጫካው ይዞት ገባ እጇን ጠምዝዞ ጣላት ፍስሃ ጫፍ ሰውነቷን ሊነካ ይፈራ የነበረውን ምህረት በአንድ ጊዜ ደፈረው በዛች በምትወዳት ምንጭ መንደር ባለጠበቀችሁ ሰው ክብረ ንፅህናዋ አጣች። ደብሬ አለቀሰች እያቃሰጠች መንገዱን ቀጠለች ትንሽ ሄዳ ዞር ብላ ያቺን የሸንበቆ ዛፍ ዱር አየቻት መሽቷል በምዕራብ በኩል ፀሃይ አጠልቃለሁ አትጠልቂም ግማሽ አካሏ ገብቶ ከራስ ዳሽን ተራሮች ጋር ትንቅንቅ ገጥማለች ቀይ ጮራዎች እግራቸውን ማዶ ዋግ ህምራ ተራሮች ላይ ዘርግተውታል ከብቶች እረኞቻቸውን እያስከተሉ ወደየቤቶቻቸው ይሄዳሉ ውሾች ከርቀት ያላዝናሉ ከልዋሬ ጎጆ ቤቶች ጭሱ ትጉልል እያሉ ወደ ሰማይ ይነጉዳሉ።

ደበሬ እንደምንም እያቃሰተች ደርሳ ለሊቱን በቅዥት አሳለፈች ውሎ አደር ግን ልቧ እየሸፈተ መጣ በሃይል የደፈራትን ምህረትን ማሰብ ጀመረች ምህረት ልቧን ወሰደው ከዛ በኋላ በድብቅ ከምህረት ጋር የስጋ ወዳጅነት ቀጠሉ ፍስሃን እዳትደርስብኝ አልፈልግህም አላችው ፍስሃ የተፈጠረውን ሁሉ አወቀ።በዚህ ብስጭት ነበር ወደ ውትድርናው የገባው ደብሬ ያለችበትን ፍቅር ያየባትን ምንጭ ራቃቸው ተለያቸው ደብሬና ምህረት ሙሉ ነጻነት አገኙ ደስ አላቸው የፍስሃ መሄድ ትንሳዔ ሆነላቸው አብረው ተጋብተው መኖር ጀመሩ።

ከኢትዮ ኤርትራ ግጭት በኋላ መንግስት የተሰውትን ለቤተሰብ ማሳወቅ ጀመረ ለፍስሃ ቤተቦች ልጃቸው ፍስሃ በጀግንነት ጀብዱ እንደተሰዋ አረዷቸው። የሰፈሩ ሰው አለቀሰ ደብሬና ምህረት ግን ተደሰቱ።ደብሬ ወደ ውሃ መቅዳት ስትሄድ ምንግዜም ቢሆን ምኀረት አብሯት አለ ፍቅር ያወራሉ ፍቅር ይቀጫሉ!ከለዕታት አንድ ቀን በተለመደው ምሽት ደብሬ ውሃ እየቀዳች ምህረት ከምንጩ አናት ላይ ቁጭ ብሎ እያለ ሸምበቆ ዛፉች ተወዛወዙ ቁምጣና ገምበሎ የለበሰ ከእነሙሉ ትጥቁ አንድ ሰው ብቅ አለ ምህረት እና ደብሬ ያዩትን ማመን አልቻሉም ከላሽንኮቭ መሳሪያውን ከምህረት ደረት ላይ ደቀነው "እኔ ማነኝ?"ተናገር አለው ፍስሃ። ምህረት በድንጋጤ "ፍስሃ ነህ..........ፍስሃ ነህ አለው".....እዎ በትክከል አውቀህኛል እኮ ምንነበር የበደልኩህ? አለ ፍስሃ የበቀል ጥሙን እስኪወጣ በችኮላ እየተቁነጠነጠ? ምህርትም ደብሬን ጨርፍ አርጎ አያት እና ዓይኑን ወደ ፍስሃ መልሶ አረ ምንም እኔ ባለጌ ሆኜ ነው"አለው። ፍስሃም "አየህ አንተ ደሲታዬን ነው የነጠከኝ እኔ ደግሞ ከእሷ ፊት ነፍስህን እነጥቀዋለሁ"አለና ደረቱን በሶስት ጥይቶች ደበደበው ደብሬ በድንጋጤ ደርቃ ቀረች ፍስሃ ፎከረ............... "የታከለ ልጅ ደም ካልመለሰ እንቅልፍ የማይተኛው የእነ እጅሬ ዘር" እያለ ፎከረ ሬሳውን ተራመደበት ተጨማሪ ሁለት ጥይት ተኩሶ ከአካባቢው ተሰወረ።





# ቅድስት

በተከረከሙ የፅድ ዛፎች በተዋበችው ፔንሲንዮን በተለመደችው ክፍል ብርድ ልብስ ውስጥ ሆነው ይሳሳቃሉ።ሸዋንግዛው ጓደኞቹ ያላገኙትን ዕድል እሱ በምላሱ አግኝቷል ምላሱ የሴትን ልጅ ጭንቅላት እና ገላ ይሞርዳል ቅድስትን የማያደርጋት ነገር የለም ልቧ ንፍር እስኪል ያስቃትና ኮብሷ ምንጥቅ እስከትል ፍቅር ይሰጣታል የማያስሮጣት ቦታ የለም እንደ እንቡጥ ፅጌረዳ ትንቡክ ትንቡክ ያለ ሰውነት ያላት ቅድስት ሁሉ ነገሯ ያምራል። ሸዋንግዛው ከእግር ጥፍሯ እስከ አናት ፀጉሯ ድረስ ይልሳታል። ጠዋት ማታ እንደ ዳዊት ዋናው ፍቅር ነው ገንዘብ ምንድ ነው እያለ እዶልዱሚታል ለቅድስት ሁሉ ነገሯ ነው ለቅድስት ሁሉ ነገሯ ዋናው ፍቅር ነው ነው። የምትማርበር ት/ቤት ስሙ ማነው ቢሏት እንኳን መልሷ ዋናው ፍቅር ነው የሚሆነው። ሸዋንግዛው ሁሉ ነገሯል ጠብቶታል እጅ ሰጥታለች ሴቶች ብልጦችምን ሞኞችም ናቸው ትልቁ ችግር ከሚባንኑት ላይ አይባንኑም የሚጠቅማቸውን ይርቃሉ ብዙ ጊዜ ተቃራኒ ነገር ያደርጋሉ።ሸዋንግዛው ምንም እንኳን ዋናው ፍቅር ነው እያለ ያዶልዱማት እንጂ የእሱ ልብ ያለው እሷን አግብቶ ቱባ ሃብታም አባቷ በደም ግፊት ሞቶ ያንን ሁሉ ሃብት በእጁ ሊያስገባ ነው።የእኔ ቆንጆ አየሽ ዋናው ንጹሁ ፍቅር ነው ሃብታሞች እኳ ሃብታም የሚሆኑት ወንጀል እየሰሩ ነው እየሰረቁ የሰው ህይወት እየቀጠፉ ነው ይላታል በእጅ አዙር አንቺ የሌባ ልጅ እያላት መሆኑን ግን ቅድስት አታስበውም። በቃ ዋናው ፍቅር ነው የውበቷ የማማሯ ሚስጥር አንዱ የሃብታም ልጅ መሆኗ ቢገባት ቅድስት ስማ ዋናው ፍቅር ሳይሆን ገንዘብ ነው እሺ ከሌለህ አመድ ነው የምትመስለው ሲኖርህ ግን ወዘናህ ያምራል ባላችው ነበር የቅድስት አስተሳሰብ ግን ዋናው መዋደድ ነው ከሚላት ፍልስፍና አልፎ ርቆ አይሄድም።

የቅድስት የአባቷ ጓደኛ ቅድስት ከሸዋንግዛው ጋር ካዛች ፔንሲዮን በተደጋጋሚ ሲገቡ አይቷቸዋል ይሄ ሁሌ ከአባቷ ቤት የማይጠፋው የአባቷ ጓደኛ አንድ ቀን ከቤታቸው ቅድስትን ጠራት እና ቅድስትዬ ለአባትሽ ከመንገሬ በፊት ለአንቺ ልንገርሽ ብዬ ነው የምትሰረው ስራ ጥሩ አይደለም ከማንም የደሃ ልጅ ጋር የትም መዋልሽ ከመዋረድሽ አልፎ አባችሽን ታሳዝኝዋለሽ አላት ስማ ዋናው ፍቅር ነው እሺ አንተ ምን አገባህ እሺ። እንኳን አንተ አባቴም በእኔ እና በፍቅሬ አያገባውም እሺ መንግስቱ ዓይኑ ደም ለበሰ እሺ እነግርልሻለሁ ብሎ ተመለሰ።

የቅድስት አባት ሽፈራው በአዲስ አባባ ከተማ የታወቀ አንቱ የተባለ ቱባ ሃብታም ነው እጁ ረጅም የፈለገውን ነገር ቤቱ ቁጭ ብሎ መፈጸም የሚችል ከኩሊው እስከ ባለስልጣን ድረስ የሚሰግዱለት የዘመኑ ቅንጡ ሃብታም ለቅድስት የልደት ቀን ከጀርመን ማርቼዲስ አስመጥቶ ለሚወዳት ልጁ ስጦታ አበርከቶላታል።ማርቼዲሷ በሳምንት አምስት ቀን ከዛች ፔንሲዮን ቁማ ትውላለች።የመንግስቱ መኖር ለሽፈራው ደጀን ነው ምንም ነገር

ስፈራውን ከሰሰው ሽፈራውም ይሄን በሰማ ጊዜ በጓደኛው ጭካኔ አዘነ ተናደደ ምግብ አቆመ ደሲታው ጠፋ ሽፈራው በፀጥታ ሃይሎች ተይዞ ወደ ማረሚያ ቤት ተወሰደ።

ድሬደዋ ቆንጆ አገር ነች ሰው እንግዳ ይወዳል ድሬደዋ ሄዶ ባይተዋር የሚሆን የለም ሸዋንግዛውና ቅድስት አገሩን ወደውታል ይሁን እንጂ የያዙትን ገንዘብ እየጨረሱ ነው ሸዋንግዛው ማሰብ መጨነቅ ጀመረ ፍቅር ቀነሰ እንደ ከረሜላ መላ ሰውነቷን ሲልሳት እንዳልነበረ በአንድ ጊዜ እርግፍ አድርጎ ተወ ቅድስት በሸዋንግዛው ለውጥ መደንገጥ ጀመረች ሸዋንግዛው ምሳ ለምጣ ብሎ እንደውትሮው ሁሉ ከተከራዩበት ትንሽ ሰርቢስ ቤት ወጥቶ ሄደ እንደ ወጣ ቀረ አልተመለሰም ፍቅሩ ዕዳ ሸክም ሆነበት ነፃነቱን የሚያገኘው በመለየት መሆኑን አመነ አባቷ ኮተታም እሷ ኮተታም እኔ ምን አገባኝ ብሎ ነበር ሸዋንግዛው ባለችበት ጥሏት የጠፋው። ሸዋንግዛው ሳይመለስ እንደወጣ ሲቀር ቅድስት ሁኔታው ገብቷት ስለነበረ ሰቅሰቅ ብላ አለቀሰች ለካ ፍቅሩ በአባቷ ሃብት ዙሪያ እንደነበረ ገባት ። ድሬደዋ ያፈራቻቸው ጓደኞች እሷት ሁኔታውን አወያየቻቸው የድሬ ልጆች መሳፈሪያ ፈለጉላትና ቅድስትን አሳፍረው ወደ አባቷ ላኳት። ቅድስት ከቤት ስትገባ አባቷ የለም ማሚ አለች እናቷን አባየስ እድሜ ለአንቺ እስር ቤት ነው አለቻት ቅድስት ተመልሳ ወጣች ጭንቅላቷ ተዛባ ሁሉ ነገር ማድረግ ስትችል ሁሉ ነገር ከእጇ ወጣ ነገሮች እንደገና ወደ ድሯቸው አይመለሱም የሸዋንግዛው ፍቅር ከህደት የአባቷ ፍቅር እስር መውረድ ሁሉ ነገር ተዘበራረቀባት ትንሽ ቆም ብላ ካሰበች በኋላ ወደ አባቷ ጓዳኛ ወደ አባቷ ጠላት ወደ እሷ አፍቃሪ ወደ መንግስቱ ቤት እየገሰገሰች ሄደች።

የመንግስቱ ቤት ፀጥታ ነግሶበታል ቤቶች አለች የሚመልስላት የለም በሩን አንኳኳች ማንሽ የሚላት የለም ቀስ ብላ ወደ ውስጥ አንገቷን አስገባች ድንገት ጮሀች መንግስቱ በራሱ ሽጉጥ ራሱን አጥፍቶ መሬት ላይ ተዘርሯል የነበረው ሁሉ እንዳልነበረ ሆኗል የሚዋደዱ አብሮ አደግ ጓደኛሞች የቅድስት አባት እና መንግስቱ በቅድስት ምክንያት እስር ቤት መንግስቱ ወደ መቃብር ወረደዋል ሁሉም ነገር ከቁጥጥር ስር ወጥቷል ልታለቅስ ያምራትና ግን ማልቀስ ይሳናታል ልትጮህ ትፈልግና ልሳኗ ይዘጋባታል ድንገት መሃል መንገድ ላይ ቁጭ ብላ ከልጅነት እስከ ዕድገቷ በቤታቸው ሲሆን የነበረውን ያንን ደግ ዘመን ወደ ኋላ አጠንጥና አስታወሰችሁ ቅድስት የነበራትን ሁሉ አጥታለች ድንገት የመኪና ጥሩንባ እንባረቀባት ቅድስት ተስፈንጥራ ወደ ዳር ወጣች ያንባረቀባት መኪና በቀስታ ወደ እሷ ተጠጋ ቅድስትዬ ቅድስትዬ የሚል ድምጽ ተሰማት የቦዘዙ ዓይኖችን ወደ ሹፌሩ ጋቢና ተመለከተች አባዬ ብላ ጮሆች ሽፈራው በፍጥነት ከመኪናው ወርዶ አቀፋት አባቴ አባቴ ካለአንተ መኖር አልችልም ጉያው ውስጥ ገብታ አልወጣ ያለው ዕንባዋ እንደ ጅረት ፈሰሰ።





# በማርያም

ዛሬ ላይ ሃኪም ካስፈራራው ወዲህ ሱስ የተባለውን ርግፍ አድርጎ ትቷል ያሁሉ ቸበርቻቻ ጫትን እንደ ጎመን የሚያንጎፍጠው ሺሻና ሲጋራን እንደ ፋብሪካ ጭስ የሚያቅቧልቀው ባቡ አስችሎት ከሱስ ጋር ተታቶ ራሱን ከስራ ጋር ለማለማምድ ደፋ ቀና ይላል።እንደ ግሪሳ ወፍ ግር እያሉ ያጅቡት የነበሩት የሱስ ጓደኞቹ ዛሬ ሁሉም ሸሽተውታል በምግባር እንደተራራቅን በጓደኝነትም እንዲሁ ብለው አድማ እንዳደረጉ ሁሉ ባንድነት ግንኙነታቸውን አቋመዋል።ያደለው ሰው በገንዘብ ሰው ይሆናል ባቡን ግን ገንዘብ በቁሙ አሰልስሎ መቃብር ሊያወርደው ጧዋት ማታ አይዞህ ይለዋል። ባቡ ሶስት ወንድሞቹንና ሁለት እህቶቹ በአሜሪካን ሃገር መኖር ከጀመሩ ጀምሮ በየወሩ ዶላር እንደ ዶፍ ዝናብ ይንዥቀዥቅለታል ሁሉም በድህነት ያሳደጎቸውን እናታቸውን ይወዳሉ እንጨት ሰብራ.........ጠላ ጠምቃ.................ጠላ ሸጣ ራሷን ለልጅ ፍቅር አሳልፋ የሰጠችው እናታቸው መቸውንም ከፍቷት ማየት አይፈልጉም የፈለገችውን ታደርግ ዘንድ በየሳምንቱ ዶላር ይልኩላታል የእናታቸው ሞግዚት ገንዘብ ተቀባይ እና ስራ አስፈጻሚ ደግሞ የመጨረሻው ወንድማቸው ባቡ ነው። ባቡን በስልክ ሲያወሩት በእንደበቱ ፍፁም ጨዋ ነው ፍፁም ለእናቱ ሃሳቢ ነው ነገር ግን ባቡ ከሚላከው ዶላር ለእናቱ ሩብን ብቻ ነበር የሚሰጥ ይህ ሲሆን እናትዬው ባቡ ገንዘቡን እንደሚያጭበረብር ጠፍቷቸው ሳይሆን እንደ መጨረሻ ልጅነቱ የመጨረሻውን የወሊድ ምጥ አንጀት እንደ ጎተተው ቀርቷል እናቱ ከልጆቹ ሁሉ አስበልጠው ይወዱታል።

መጠጡ ፣ ጫቱን ፣ ሲጋራው ፣ ሺሻው ፣ ሴቱ እሱን እንዳይጎዳው እንጂ በዚህ ሁሉ የሚያጠፋው ለእናቱ አይታያቸውም ባቡ የዋለበት ቤት ያመሸበት ቤት ሰርግ ነው ባቡን ከአዝማሪ እስከ ኮማሪ ያውቁታል። አዝማሪዎች ይገጥሙለታል ይዘፍኑለታል ኮማሪዎች ከከሸን ዶሮ ወጥ ገላቸውንና ቅቤ ለራሱ ሳይቀር ይቀቡታል ብቻ ባቡ የጎንደር ከተማ ንጉስ ነው በባቡ እጅ ከባለስልጣን እስከ ጫማ ጠራጊ ሊስትሮ ያልተጋበዘ የለም።

ባቡን በፍቅር አንበርክከው በመዳፋቸው ስር አውለው ፀንሰውና ወልደውም ተጋብተው በአንድ ጣራ ስር አብረው ለመኖር ከተማሪ እስከ ሴት አዳሪ ተደባድበውበታል። ባቡ ያናገራት ሴት ልጅ አይደለችም ሰላም ብሏት ያለፊት ትንዘፈዘፋለች ባቡ ኢንቨስተር አይደለ በትምህርቱ ተመርቆ በዕውቀቱም የሚኖር አይደለም ባቡ ዕድል ፊቷን አብርታለት በጠቀመጠበት እናቱ ላይ ዶላር የሚፈስበት የእግዚሃብሄር ምራቅ አከታ ያረፈበት ዕድለኛ ልጅ ነው።

እናቱ እማሆይ ሃረገወይን ትልቁ ወጪያቸው በአመት አንድ ጊዜ የሚዘከሯትን ግንቦት ማርያምን ነች።ለግንቦት ማርያም ሲሆን ልጆች ስለሚያውቁ በወርሃ ግንቦት የሚላከው ዶላር

ታደሰ ከራሱ ይልቅ ለምስኪን እንጀራ እናቶቹ ያዝናል እንዚህ የኢኮኖሚ ጥገኛ ሴቶች መተዳደሪያ ቢኖራቸው ኖሮ ሚስት ሆነው ከአባቱ ጋር አንድ ቤት ውስጥ መኖር አይደለም ለደቂቃም እንኳ ቆመው እያናግሯቸውም ነበር ሆኖም ግን አባቱ በሚስትነት የሚያመጧቸው ሴቶች ችግረኞች እና መድረሻ ያጣ ናቸው ደካማ ጎናቸውን ተጠቅመው እንደ ግዥ ዕቃ እንደፈለገ ያደርጋቸዋል።

ሰራተኞቻቸውን ሲያሰናብቱ እንጂ የሰሩበትን የለፋበትን የላባቸውን ሳይከፍሉ ነበር የሚያባርራቸው አባቱ የጎረቤት ድንበር መግፋት ሰውን ማስፈራራት በመንግስት መስሪያቤቶች አካባቢ ጉዳያቸውን በጉቦ ማስፈፀም ይወድ ነበር።

ታደሰ እንደምንም እየታመመ ትምህርቱን ጨርሶ ከዛ ሁሉ መከራ ወጥቶ ራሱን ችሎ ለብቻው መኖር ጀመረ ሆኖም ግን ህሊናው ዕረፍት ሊያገኝ አልቻለም ያሳለፈው የልጅነት ህይወቱ ምንጊዜም ህሊናው ውስጥ ያቃጭልበታል ጆሮውን ግጥም አድርጎ ይዞ ዓይኑን ይጨፍናል እንደ ገና ይገልጣል ምንአልባት የአባቱን አኗኗር የሚኖር እየመሰለው ሚስት አግብቶ መኖርን ይፈራል ስለሆንም ብቸኝነትን መረጠ ጩኸት ለቅሶ እሪታ አይወድም ፀጥታ የሰፈነበት ሰላማዊ ሰፈር ይወዳል በአንዳንድ ጉዳዮች ከሰዎች ጋር ይጋጫል ቁጡ ነው ትዕግስት የለውም በሰዎች ላይ የሚያየው ትንሽ ስህተት ሁሉ የአባቱን ትልቅ ስህተት ያስታውሰዋል ያረገዘች ያዘለች ሴት ባየ ጊዜ ከፉኛ ልቡ በሃዘን ይናጣል ህይወታቸው የተመሳቀለ ሆኖ ይሰማዋል ታደሰ እንዲሁ እንዲህ እያለ የብቸኝነትን ህይወት ለተወሰኑ አመታት ኖረ ሆኖም ግን በመጨረሻ የተጠራቀመበት ሁሉ ገነፈለበትና በደንገት አእምሮውን ስቶ ለእብደት ተዳረገ።

እብዱ ዛሬ የፈለገውን በጩኸት እየተናገረ ይወጣለታል ሲፈልግ ይጮሃል ሲፈልግ ይጨመታል አእምሮው የሚያስታውሰው ውስጡን የሚረብሸው ነገር የለም





# እርቅ

በምስራቅ ጎጃም ደጀን አፋፍ ኪዳነ ምህረት ላይ በእድሜ ጠና ያሉት....አባ ደጉ እና አባ ተሻለ...ጓደኝነታቸው ከልጅነት እስከ እርጅና አብሮ ዘልቋል...አብረው ውለው ሲመሽ ይለያያሉ...የድሮ ትዝታቸውን እያወሱ ....በምቱት እየቆዘሙ...የኖሩትን ለኋሎሽ ያስታውሳሉ።

አሁን ጊዜው ክረምት ነው። ነፍራቃ ክረምት ...አልቃሻ......ወደ አባይ ወንዝ መውረጃ አፋፍ ላይ ሆነው ማዶ ነጭ አረፋ እየደፈቀ የሚወርደውን የአባይን ወንዝ እና ዙሪያ ገቡን ጭል ጭል እያደረጉ እንደ ህፃን ልጅ ሽንት ውሃቸውን የሚረጩትን ሸንተረሮች ከሚታዩበት መካከል ቦታ ላይ ተቀምጠዋል። ፀሃይዋ እንደምንም ከዳመናዎች አፈትልካ እየተሹለከለከች በስርቆሽ ብርሃኗን ትረጫለች...ግን አትሞቅም። በክረምቱ በብርዱ ተሸንፋለች ፀሃይን የምታከል ጀግና ስንቱን አገር በረሃ አድርጋ ምድረ በዳ እንዳላደረገች...ስንቱን በክርኗ እንዳልደቆሰች....እሷን የሚያክል ጀግና ዛሬ በክረምቱ ተሸንፋ...ቁሩን መቋቋም ተስኗት አቅም አንሷት ...ትንፋሽ አጥሯት...የሞት ሽረት ትፈራገጣለች።

ሁለቱ ሽማግሌዎች ጋቢ ተጀቡነው ተከናንበዋል። ብርድ ጥፍሩን አሹሎ አይኑን ጎልጉሎ ሲመጣ ጋቢ አላስጠጋህ ይለውና ገፍትሮ ይጥለዋል....። ሽማግሌዎቹ ከድሮ እስከ ዘንድሮ ስለ ነበረውን እና ስለ አለው ነባራዊ ሁኔታ ይወያያሉ

እየ ጉድ አሉ አባ ተሻለ....ድሮ ክረምቱ ስድስት ወር ይቆይ ነበር። መሬቱ ሁሉ ውሃ ይፈልቅ ነበር። ስንዝር መሬት ተቆፍሮ ጎተራ ሙሉ እህል ይዛቅ ነበር። አሁን ጊዜው ከፋ። አሉ አባ ተሻለ በዱላቸው መሬቱን እየቆረቆሩ። የዘመኑ ክረምት ከዘመኑ ጋር ዘምኖ ደመናው ለይስሙላ ጠቋቁሮ...የውሸት ጉርምርምታውን አምባርቆ ምራቅ ታክል ዝናብ ጠብ አድርጎ ይሄዳል። ሰውም በዛ....ዛፉ ሁሉ አለቀ...አገር ምድረ በዳ ሆነች። የእኛም ሃጢያት በዝቶ እግዜር ጨከነብን። ብለው አይናቸውን አባይ ማዶ ሸንተረር ላይ ተከሉ።

አባ ደጉ ቀበል አደረጉና....ችግሩ ያለው ከእኛ እና ከእግዜር ላይ አይደለም። እግዜር እማ አዛኝ...ቸር ነው። ሰይጣን ነው ሚያምሰን....ሰይጣን ነው ሚያቦካን ሚጋግረን። ሰይጣን እኛን ጠቅልሎ ወደ ራሱ ግዛት ጨርሶ ሳይወስደን አይተኛም።ስራውን እየሰራ ነው። ሰይጣን እኮ፡-

ገበሬ ሁኖ የሰው ደንበር እየገፋ ነው....ጉልበተኛ ሆኖ የሰው ሚስት እየደፈረ ነው....ሽፍታ ሆኖ የሰው ገንዘብ እየዘረፈ ነው...ሴተኛ አዳሪ ሆኖ እየዘሞተ ነው....ሹመኛ ሆኖ ጉቦ እየበላ ነው....ነጋዴ ሆኖ እያጭበረበረ ነው....ሰይጣን ምን ማያደርገው ነገር አለ....በየ ጉያችን ጠንቋይና ደብተራ ኮልኩሎልናል....ለሰይጣን አድር ባይ በሽ ሆነለት....ያጎነብሱለታል....መስዋዕት ይሰጡታል...ያቋድሱታል....ያሽሞነሙኑታል....ምን አለፋህ

አገሩን በሙላ ብጥብጥ ያደረገው ሰይጣን ነው። አሉ አባ ደጉ ጋቢያቸውን እስከ አፍንጫቸው እየተከናነቡ።

አይደለም....አይደለም አሉ አባ ተሻለ። ቁርጥ ባለ ትንፋሽ። ፊታቸውን ወደ አባ ደጉ መልሰው እንደገና መልሰው አይናቸውን ጭስ ወደ መሰለው አባይ ማዶ ጋራ ላይ እየተከሉ። ሰይጣን ምን አቅም አለው ብለህ ነው....ሰይጣን ምን ሃይል አለው....የእኛ ሃጢያት ሲበዛ እግዜር ተቆጥቶ ጨክኖ እየቀጣን ነው...እኛም አበዛነው...እሱም አበሳችን አበዛው.....እርግጥ ነው እግዜር ቸር...አዛኝ....መሃሪ ነው። አሁን ግን አምርሯል መሰለኝ....ቅጣታችን በዛ.....። አሉ አባ ተሻለ። የኑሮው ሁኔታ ከዕለት ዕለት እንዴት እየከበደ እንደመጣ በሃሳባቸው እያብሰለሰሉ።

ቄሰ ገበዝ ፈንቴ ከሁለት ሰዎች ጋር ከኪዳነ ምህረት እርፍደው በቀጭኗ መንገድ ይጓዛሉ። ረባዳውን መሬት አልፈው ወደ አፋፉ እየተጠጉ ሲሄዱ የእነ አባ ደጉ ጭቅጭቅ ተሰማቸው...አፋፉ ላይ እንደወጡ ተያዩ። እንደምን አደራችሁ አሉ መንገደኞቹ። እመስገነው ብለው አባ ደጉና አባ ተሻለ መስቀል ለመሳለም ወደ ቄሰ ገበዝ ፈንቴ ጎንበስ ብለው ቀረቡ። ቄሱም አሳልመው በእግዜር ቁጭ በሉ ብለው ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ አደረጉ።

ከመንገደኞች አንዱ አጠር ያለው ሰውየ...ወጋችሁ እኮ ኪዳነ ምህረት ድረስ ይሰማል.....በዚህ በማለዳ እንዴት ያለ ወግ አገኛችሁ? ብሎ ጠየቀ። አባ ተሻለ ቀደም አሉና የክርክር ርዕሳቸውን አጠር አድርገው አስረዷቸው። አጠር ያለው ሰውየ እግሮቹን አጠላልፎ ሙሉ ሰውነቱን በዱላው ምርኩዝ ላይ ተደግፎ ከንፈሮቹን በእጁ እየጠራረገ ፈጠን ብሎ አስተያየት መስጠት ጀመረ። በእርግጥ የሁለታችሁም አበባል ትክክል ይመስለኛል.....የሁለታችሁም አባባል ሂዶ ሂዶ መቆሚያው አንድ ነው። ምክንያቱም እግዜር ለሰይጣን ስልጣን ሰጠው...ሰይጣን ደግሞ እኛን ያሳስታል....እኛ ስንሳሳት እግዜር ይቀጣናል። የተያያዘ የተሳሰረ ነገር ነው። አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ የነበረው...ያለው....እና የሚኖረው ሂደት ይሄው ነው። ቀጠል አደረገና እጭሩ ሰውየ... የሚሆን ከሆነ እና ከተሳካ መፍሄሃው ቀላል ነው አለ ምርኩዙን ከግራ ብብቱ ወደ ቀኝ ብብቱ እያዛወረ። መፍትሄው ተግባራዊ ከሆነ ደግሞ በሰማይ የገነም ቤት ይዘጋል። ....በምድር ደግሞ ፍቅር ሰላም ነግሶ.....ችግር መከራ ይወገዳሉ። አለ እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ በልበ ሙሉነት።

በእጀ አሉ አባ ተሻለ....ምንድን ነው እልከ መፍትሄው ...ብለው ጠየቁትና ሁሉም በጉጉት መልሱን ይጠባበቁ ጀመር።

መፍሄሃው እማ አለ አጠር ያለው ሰውየ ሁሉንም በአይኑ እየቃኘ። እግዜርን እና ሰይጣንን በሽማግሌ ለእርቅ አቅርቦ....ሰይጣንን ጌታየ ማረኝ ብለህ ከእግዜር እግር ውደቅ ማለት። እግዜርን ደግሞ ምሬሃለሁ....ይቅርታ አድርጌልሃለሁ...ብሎ ምህረት እንዲያደርግለት ማድረግ። ከዛ በኋላ በአንዲት ላም ወተት.....በአንድ እግር ሽንብራ ሁላችንም በቅቶን ጠግበን በደስታ እንኖራለን አለ። እግሩን ቀያይሮ እያቆላለፈ።





እህ....አንተ እንዴት ያለህ ቀልደኛ ሰው ነህ....እግዜር እና ሰይጣንን የት አግኝተህ ...እንዴት አድርገህ ነው ምታስታርቅ....አሉ አባ ደጉ ከንብንባቸውን ከራሳቸው ላይ እያወለቁ።

ቄሰ ገበዝ ፍስሃም ነጠቅ አደረጉና....እግዜርን ማግኘት ነው እንጅ ሚከብደው ሰይጣንን ማግኘት ቀላል ነው አሉ።.....ሲናገሩ በሸራፋ ጥርሳቸው መሃል ምራቃቸውን እየረጩ።

አባ ደጉ ቀበል አድርገው....በቄሰ ገበዙ አብደት እየተገረሙ....ሰይጣን እኮ መንፈስ ነው። ሰይጣንንስ የት ነው ምናገኘው አሉ....ትንንሽ አይኖቻቸውን በቁጣ እያፈራገጧቸው።

ቄሰ ገበዙ በሸራፋ ጥርሳቸው ፈገግ አሉና....ሰይጣንን አሁን ላሳያችሁ!....አሉ እና ...ትንፋሻቸውን አቁመው... ሁሉን በጥያቄ መልክ አፈጠጡባቸው። ሌሎች በግርምት እርስ በርስ ተያዩና.....ሰይጣንን ከየት አምጥተህ ነው ምታሳየን ...ነው ደፈተርከ....አሉ አባ ተሻለ ከሌሎቹ ሰዎች ቀድመው

አባ ተሻለ....አሉ ቄሰ ገበዝ ፈንቴ....ትልቁ አጋንንት ይሄው ከእኛ ጋር ተቀላቅሎ....አሉ እግዜር እና ሰይጣን ይታረቁ ብሎ ወደተናገረው ሰው ሌባ ጣታቸውን ቀሰረው።

# ምስጥ

በድሮ ጊዜ ነበር....የፍጡራንን ሁሉ የበላይ የሆነውን ሰው እየበሉ የሚኖሩት..ጥቃቅን ነፍሳቶች መንደር...ችግር ገብቶ...አገር ደርቆ...የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ...ሁሉም መንነው ወደ ስደት የወጡት....እነ ትኋን...ቁንጫ...ቅማል...ሙጀሌ....ምስጥ....የወባ ትንኝ....ወዘተ....ሁሉም በርሃቡ ተልፈሰፈሱ...ጉልበታቸው ራደ...አንጀታቸው ታጠፈ....ጉሮሯቸው ደረቀ። ፈጣሪን አማረሩ....መጨረሻ ስደትን መረጡ...እነሱ ያሉበት አካባቢ ሳሩ አድጎና ለምልሞ እነ ጎሽ ...ድኩላ እና የሜዳ አህያ ...ሳሩን በልተው ሆዳቸው ዚጥ ብሎ ሞልቷል...ቀና ሲሊ የፍራፍሬ መዓት ተንዠርርቆ እነ ጦጢት ጠግበው ይወራወሩበታል....ወደ ጎን ሲያዩ እነ አንበሳ ነብር የሜዳ አህያውን...ድኩላውን በልተው አትርፈው...ትርፉን አሞሮች ሲጎትቱት አዩ...እነሱ ግን ተርበዋል....የእነሱ ምግብ እዛ የለም...ቀን ጨልሞባቸዋል...እንዲህም አሉ....ወይ እንደ እነ አንበሳ ነብር...ጥርስ እና ጥፍር ብትሰጠን...የሜዳ አህያውን...ድኩላውን...ጎሹን...እየገነደስን...እየዘለዘልን እንበላ ነበር....የእኛን ምግብ ደም አደረከው...ደም...የሰው ደም።...ምነው ፈጣሪ ሳልጠፋ ምግብ...ወይ ደግሞ እንደ እነ ጦጣ ጅንጀሮ አድርገህ ፈጥረህን ቢሆን ኑሮ.....ከተንዠረቀቀው ብርቱካን...ሎሚ....ሙዝ...ፓፓያ...አቦካዶ...መንደሪን...እየገመጥን እንበላ ነበር....የእኛን ምግብ ግን ደም አደረከው...ደም .....የሰው ደም። ወይ ደግሞ እንደ ከብት...ፍየል...በግ አድርገህን ቢሆን ኖሮ....የለመለመውን ሳር ግጠን...እፎይ ብለን...ተመስገን እንልህ ነበር...የእኛን ምግብ ግን ደም አደረከው....ደም...የሰው ደም.....ወይ እንደ ጭልፊት....ወይ እንደ ጥንብ አንሳ አድርገህ ፈጥረህን ቢሆን ኑሮ....ጥንባችን ለቅመን...ጫጩታችን ዘርፈን እንበላ ነበር....የእኛን ምግብ ግን ደም አደረከው....ደም የሰው ደም....ወይ አሳ አድርገህ ፈጥረህን ቢሆን....ውቅያኖሳችን ውስጥ...ሃይቃችን ውስጥ....ወንዛችን ውስጥ...እርስ በዕርስ እየተበላላን እንኖር ነበር....የእኛን ምግብ ግን ደም አደረከው...ደም....የሰው ደም.....ወይ ቅንቡርስ ብታደርገን አፈር እየበላን እንኖር ነበር.....ወይ ሰው ብታደርገን....እየተፋጀን....እየተወሻሽን....እየተገዳደልን...እየተቀማማን....እንኖር ነበር....የእኛን ምግብ ግን ደም አደረከው....የሰው ደም....ሰው ደግሞ እንኳን ደሙን...ቆሻሻውን አይሰጥም....እንኳን ለእኛ እርስ በርሱም አይሰጣጥም...። አሉ።.... ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ተጋቡ.....ወደየት አቅጣጫ እንሂድ....ሰው ያለበት አቅጣጫ... ተባባሉ...ግማሹ ወደሰተሰሜን እንሂድ ይላል....ግማሹ ወደ ደቡብ እንሂድ ይላል...ግማሹ ወደ ምስራቅ....ቀሪዎች ወደ ምዕራብ እንሂድ አሉ። በዚህ የተነሳ ጭቅጭቅ....ጥል





መጣ...ተፋጁ...እኔ ያልኩት ነው ትክክል....እኔ ያልኩት ነው...ተቧጨሩ...ተናከሱ....ሁሉም ወደየመረጡት አቅጣጫ ነጎዱ። ትኋን እና ቁንጫ ለብቻቸው አንሾካሸኩ....ቢሞቱም ቢድኑም አብረው ለመሆን ወሰኑ....በዚህ ጊዜ ቁንጫ የሆነ ነገር ቅር አለውና የሆነ ሃሳብ እንዳለው ለትኋን ነገረው...ትኋንም ሃሳብህ ምንድን ነው አለው....ቁንጫም ለሁሉም ነገር እንዲቀናን....መንገዳችን ሰላም እንዲሆን...የዕለት እንጀራችንም ቶሎ እንዲሰጠን....ከከፋ ነገር እንዲሰውረን....ቀናውን መንገድ እንዲመራን ....እንፀልይ...እኔ እና አንተ ደግሞ ላንካካድ...ያገኘነውን ተካፍለን ልንበላ...አንተ ስትተኛ እኔ ልጠብቅህ....እኔ ስተኛ አንተ ልትጠብቀኝ....ቃል እንገባባ አለው.....ትኋንም ትንሽ ካቅማማ በኋላ በሃሳቡ ተስማማ። ምስጥ ቀስ ብሎ የሁሉን እንቅስቃሴ ያይ ነበር....ትኋን እና ቁንጫ ሲመካከሩ ሰምቷል።....ምስጥም ቀስ ብሎ ወደ ትኋን ተጠግቶ...ትኋንን ያደንቀው....ያሞግሰው ጀመር.....ትኋንየ አለው ምስጥ... ደስ በሚል ያነጋገር....አንተ እኮ እንደማንም ሆዳም አይደለህም....ቢያስፈልግህ ሳትበላ ...ሳትጠጣ...ለብዙ ጊዜ መቆየት ትችላለህ....ደግሞ ደፋር ጀግና ነህ...አትፈራም...ሰዎች እንኳ አንተን ነክተው....እጃቸውን ወደ አፍንጫቸው ነው ሚወስዱት...ሽታህ ልዩ ነው....ይሄ አለ እንጅ....ቁንጫ የሚሉት ወዝ የለሽ አመዳም....ባንተ ተጠግቶ ....እራሱን ብልጥ...አንተን ጅል አድርጎ ሊጠቀምብህ ጠጋ ጠጋ ይላል....ደግሞ አደብ የለለው አብድ ስለሆነ ወዲህ ወዲያ ሲዘል አንተን ነው ሚያስዝህ....ይሄ ሌባ....አንተን አስይዞ እሱ ያመልጥ እና.....ከዛ ብቻውን እየተመላለሰ ሊበላ ነው....እንዳታምነው...ይሄን ወዝ የለሽ.....የምታገኘውን ደም እስኪያልቅ ድረስ መጥምጦ....ምንም ነገር ማስተረፍ የለብህም....አለውና...ለማንኛውም እኔ አብሬያችሁ እሄድና ቀስ ብየ የሚያደርገውን ሁሉ እከታተላለሁ ...አለ ምስጥ...የትኋንን ሆዳምነት ጠንቅቆ ስለሚያውቅ እንዴት እንሚጠቀምበት እያሰበ.....ትኋንም በምስጥ ምክር....ተደሰተ...አመሰገነው....ዝም በለው ይሄን አመዳም.....ብሎ....ምስጥም አብሮ ጉዞ ጀመረ።....የምስጥ ሁኔታ ያላማረው ቁንጫ ቀስ ብሎ ወደ ምስጥ ተጠጋና...ይሄውልህ ትኋኔ....ምስጥ ምንጊዜም ምስጥ ነው...የፈለገ ነገር ቢልህ እንዳትሰማው....ይሄኔ ለራሱ ጥቅም በእኛ ላይ ሁኔታዎችን ሊያመቻችብን ነው። አለ.......ትኋን ለቁንጫ ምንም መልስ አልመለሰለትም።መንገዳቸውን ቀጠሉ.....ብዙ እንደተጓዙ ወንዝ ሞልቶባቸው አገኙ....ቁንጫ ዝል ብሎ ወንዙን ተሻገረ.....እየኸው ይሄን ራስ ወዳድ....ካህዲ...ጥሎን ተሻገረ እኮ....አለው ምስጥ ለትኋን....ትኋንም....ቆይ ተወው ግድ የለም ....ይልቁንስ እንዴት ነው ምንሻገረው አለ ትኋን....እየጨነቀው....ምስጥም ፈጠን ብሎ አይዞህ አሻግርሃለሁ አለው....ትኋንን በውለታ እየያዘው መሆኑን ሲያውቅ ልቡ ጮቤ እየረገጠ። ምስጥ አንድ እንጨት እየጎተተ መጣና...በወንዙ ማዶ እና ማዶ አጋደመለት። ....ትኋን ተሻገረ....ምስጥንም ውለታ መልሸ ያድርገኝ አለው።..... ተጉዘው ተጉዘው በአንዲት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ብቻዋን የምትኖር...በደም ማነስ የታመመች ሴትዮ ደከማና ሰልስላ ተኝታ አገኟት።....ደስ አላቸውና እንዴት እንደሚገቡ ዘየዱ...ምስጥ ለትኋን መግቢያ የሚሆን የቤቱን ግድግዳ በረበረለት....ወደ ትኋን ጀሮ ጠጋ ብሎ ቁንጫን

ደረሲው ከዚህ በፊት ያሳተመው
* አርባ ጅራፍ የግጥም እና
የአጫጭር ትረካዎች መድብል



# አጀብ

እንዲያው ይሄ ቀልቤ.....ስንቱን ያስታውሳል
ትላንትን እያየ...አደቤን ይነሳል
ከቆረጠው እሸት...ካሻቸው ዘለላ
ከጠነቆለው ማር...ከዋጠው ወለላ
ከለቀመው ፍሬ....ካንጠባጠባቸው
ከቀማመሳቸው....ከጠረጠራቸው
ዶለኝ ወስዶ ቀልቤ...ጎትቶ ከኋላ
የድሮውን ሳስብ...እንዴት አሁን ልብላ
..........አጀብ
የዘመኑ ፍጥነት....የጊዜው ሩጫ
እድሜ መንገደኛው...ጠፋበት አቅጣጫ
.......እስኪ ይሁና
ትዝታም ይኮምኮም....አንጀት ከጠገነ
ቀልብ አደብ ከገዛ....በነበር ከሆነ

ዋጋ $ 10.00